የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

**ሚያዝያ 16፣ 1999ዓ.ም.**

# ውድ ታዳሚዎች

Ethiocurrent event Assimba — Voice Room የወቅቱ የሀገራችንን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ በመመርኮዝ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች በአጀንዳ መልክና የተለያዩ እንግዶችን በመጋበዝ ለመወያየት፣ ለመማማርና ግንዛቤ ለመጨበጥ ከምናደርገው ጥረት በተጨማሪ ከአሉት ዝግጅቶች አንዱ በየወሩ ሊቀርብ የታሰበ የሥነጽሑፍ ቀን አንዱ ነው።

ይህንን የአሲምባ ሩም የሥነ ጽሑፍ ቀን ምክንያት በማድረግ በዛሬው ዕለት ለመጀመሪያ ጊዜ ይህን ዝግጅት ስናቀርብ ታዳሚዎቹም ሆኑ ሌሎች በቀጣይነት በሚልኩት ፣ በሚሰጡት፣ ሃሳብ አስተያየት በመታገዝ የሌሎችን የኪነጥበብ ሰዎችንና ታዋቂ ግለሰቦችን ሥራ ለማቅረብ በሩን ይከፍት ዘንድ፣ ቀጣይ ዝግጅት ይደረግ ዘንድ በማሰብ ነው።

በዛሬው ዕለት የምናቀርብላችሁ ሀያሲ፣ ገጣሚና የሥነጽሑፍ ተመራማሪውን የአቶ ደበበ ሰይፉን ሥራዎች ይሆናል። ይህ ዝግጅት የተቀናበረው አቶ ደበበ የዛሬ 7 ዓመት ሚያዝያ 16 ቀን 1992 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየበት ጊዜ ጀምሮ ሥራውንና ታሪኩን በተለያየ መገናኛ መንገድ (ሬዲዮ፣ ጋዜጣ፣ መጽሔት፣ ቴሌቪዥን፣ በመድረክ፣ ወዘተ.) ከአቀረቡ አፍቃሪዎቹ የተሰባሰበ መሆኑን እንድትገነዘቡልን እንጠይቃለን።

በዚህም መሠረት በአቶ ደበበ ሥራዎች ላይ ተጽፈው ለአንባቢያን ከቀረቡና ለዚህ ዝግጅት እገዛ ያደረጉትን ምስጋና እናቀርባለን። ከነሱም፦

አቶ ከበደ ገብረሃና፣ አቶ ገዛኸኝ ጌታቸው፣ አቶ መሠረት አታላይ፣ አቶ መሠረት ዓለሙ፣ አቶ ከበደ ደበሌ ሮቢ፣ አቶ ሀብታሙ አሰፋ፣ አቶ ታደለ ገድሌ;።

ይህ ዝግጅት የነኝህንና የሌሎችን አፍቃሪዎቹን ሥራ በማካተቱ እጅጉን ሊመሰገኑ ይገባል።

የጋሼ ደበበ ተማሪ ግርማ ደገፉ ለዚህ ዝግጅት መቀናበር በአደርግው ትልቅ እገዛ ከፍትኛ ምስጋና ይገባዋል።

በሌላም በኩል በተለያየ መንገድ ለዚህ ዝግጅት አስተዋጽዎ ያደረጋችሁት ሁሉ ምስጋና ይድረሳችሁ። እናመሰግናለን።

ዝግጅቱ በአቶ ደበበ ሥራዎች በቀረቡና በራሱ አንደበት በተነበቡ ሥራዎቹ እየታገዘ ይጀምራል። በምዕተ ዓመት አንዴ የሚገኝ የተባለለት ግጥሙ «ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ» የመጀመሪያው ክፍል ውስጥ ይካተታል።

የአቶ ደበበ ሰይፉ ወንድሞች ስለ ቤተሰባዊ ሕይወቱ ያወጉናል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

ስለ ጋሼ ደበበ ሰይፉ የሚያውቁ ግለሰቦች (ተማሪዎቹ፤ የሥራ ባልደርቦቹ፤ ወዘተ. የነበሩ) አስተያየት ጊዜ ተሰጥቶታል።

ቀጣይ የአቶ ደበበ ሥራዎች ይቀርባሉ።

ከቤቱ በተለይ የአቶ ደበበን ሰይፉ ሥራ የሚያውቁና በአዳመጡትም የራሳቸውን ሃሳብ ማካፈል ለሚፈልጉ መድረኩ ክፍት ይሆናል።

በመጨረሻም በአጠቃላይ ዝግጅቱ በዚህ ቤት የመጀመሪያ እንደመሆኑ በቀጣይነት የሌሎች ኢትዮጵያውያን ሥራም ለማስተዋወቅ ይረዳ ዘንድ ከቤቱ አጠቃላይ አስተያየት ይስተናገዳል።

ዝግጅቱን ከጅምሩ ትኩረት ተሰጥቶት መከታተሉ ምን ያህል ስለ አቶ ደበበ ሰይፉ ሥራ ግንዛቤ ይሰጣልና በጥሞና እንድንከታተለው ግድ ይላል። በተለይ ግጥሞቹን ጆሮ ሰጥቶ ለማዳመጥ፤ ሃሳብን አሰባስቦ መከታተልን ይጠይቃል።

አንዳንድ ቦታ በተለይ እየዘገዩ የሚገቡ ታዳሚዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ስለማን እንደሚተረክና እንድሚወራ ግንዛቤ ለመስጠት  ይረዳ ዘንድ በተለይ የአቶ ደበበ ሰይፉ አጭር የሕይወት ታሪክ መደጋገሙን ከዚህ እይታ ትገነዘቡልን ዘንድ አደራ እንላለን።

የተከበራችሁ ታዳሚዎች ከሁሉ አስቀድመን አቶ ደበበ ሰይፉን ለማስታወስ የአንድ ደቂቃ የህሊና ጸሎት እናደርግ ዘንድ በአክብሮት እጠይቃለሁ።

እናመሰግናለን። ዝግጅቱ ይቀጥላል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

<u>የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም</u>

# ደበበ ሰይፉ ካረፈ በርግጥ ሰባት ዓመት ሞላው ?

# የታላቁ «መብረቅ» መዘክርታ

እንደ ከብደ ደበሌ ሮቢ አባባል ይህንን ዝግጅት ስናቀርብ የሚፏጥጠን ቅሬታ ቢኖር ፦ «በእኛ አገር የአንድ ትልቅ ሰው ሥም የሚነሳው በህይወት ሳለ ሳይሆን፤ ከሞተ በኋላ ነው» ከሚለው ተደጋጋሚ «ድርትራች ቡትቶ» በተሰፋው ከረጢት ውስጥ አንድ ጠጠር በመጣላችን ነው እንጂ፦ ለደበበ ሰይፉ ይህ ትንሽ ነው።

ልክ የዛሬ ሰባት ዓመት ፤ ታላቁ «መብረቅ» «አረፈ»

ማክሰኞ ፡ ሚያዝያ 17፣ 1992 ዓ.ም. ቅዱስ ዮሴፍ ጀርባ አፈር እቅፍ ከመከተቱ በፊት ለሰባት ዓመታት የአልጋ ቁራኛ ሆኖ ቆይቷል። አንድ ቀን፦ የፈውስ አክሊል ጭኖ ከዚያ ድሁር አካሉ ሲወጣ የርሱ የማይመስለውን መብረቅ ድምፁን እንሰማለን ብለው ተስፋ ያደረጉ እጅግ ብዙ ነበሩ። እርሱ ግን ተስፋ መቁረጥን ተስፋ እንዳደረገ በዚያው ሄደ። «የተስፋዬ ዛፉ» እያለ ወደ ጥንታዊ ተፈጥሮው ተመለሰ።

## የተስፋዬ ዛፉ

የተስፋዬ ዛፉ ሲከረከም ቅርንጫፉ፤
ሥሩ ሲነቃቀል
ሲበጠስ ሲፈነገል፤
አንጥሬ ደርቤ ማቄን
ዘንግቻት እንቁጣጣሽን
ዐድይ አበባ ዐደዬን፤
በድቅድቁ ተቀመጥኩኝ
ላለማሰብ እያሰብኩኝ፡
የልቤን ልበ-ባሻነት ገሰፅኩኝ
ላለማሰብ እያሰብክኝ
ተስፋ መቁረጥን ተስፋ አደረኩኝ።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ
ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

ስድሣ ሚሊዮን ሆነን ፤ ምዕተ ዓመት አምጠን አንዴ የምንወልደው ዓይነት ኃይል አጣን። ያንን ግዙፍ ሰብዕና ሞት ነጠቀን። ትልልቅ ወንጀላቸውን ተሸክመው በንፁሃን ስስ «የድክመት» ክንፍ ሥር ለመሸሸግ የሚሞክሩ ልበ ድፍን መሰሪዎችንና ተፈጥረው ያላለቁ ደናቁርትን በብርቱ ብዕሩ መዋጋት የማይታክተው ትልቅ ሰው አጣን። «የአባትህ ልጅ» እንዳለ ፤ «ቋጥኙ»ን እንደዘመረ፤ «ጥሬ ጨው፦ ጥሬ ጨው...ጥሬ ጨዋዎች»ን እርቃን እንዳስቀረ፤ «እሱ ነው እሱ»ን እንደቋጠረ... አሸለበ።

## እሱ ነው - እሱ

እሱ ነው - እሱ
ዓይን ባይኖረው
ለምን ብርሃን ኖረ እሚለው፤
እግር ባይኖረው
ለምን መንገድ ኖረ እሚለው፤
እሱ ነው - እሱ
ከቀናቱ
ፀሐይቱን የሰረቀ ።
በመንገዱ
አሜከላ ያጸደቀ ።

ታላቁ «መበረቅ» አለፈ፤ ደበበ ሰይፉ አረፈ። ከደግነቱ ፤ ከታላቅ ተሰጥዎው ፤ ከነጥልቅ እውቀቱ ፤ ከነብሩኅ ልቡ ፤ ከነውብ ተፈጥሮው ፤ ከነ«መብረቅ» ድምፁ ፤ ከነስል ገለፃው...ተከተተ። ለፍቅር-ለውበት-ለእውነት...እንደቃተተ፤ እንዳቃሰተ...እብስ አለ። ፍቅር እንዳማጠ፤ ውበት እንዳቋተ፤ እውነት እንዳጋተ...፤ ጥበብ እንዳማጠ ፤ አምጦ-አምጦ...፤ አምጦ አመለጠ። እንደማይቀር እንግዳ በናፍቆት በሚጠብቀው እንጂ «በውል በማያውቀው» ፍቅር ልቡ እንደነደደ ፤ በሚናፍቀው እንጂ እንዲህ ነው እንዲያ ነው ብሎ በማይገልፀው ናፍቆት እንደተቃጠለ...«አንዲት ቅፅበት ብቻ» ብሎ ቃትቶ - ቃትቶ...ሞተ።

ጋሽ ደበበ ይናገራል፦ «ለአንዲት ቅፅበት ብቻ» ይላል፦

## ለአንዲት ቅጽበት ብቻ

እስቲ የማነው ጉልበት
የሰው የአማልክት
ሊሰጠኝ የሚችል የደቂቃ ዕረፍት ?
ከእውነት - ፍቅር - ውበት እማወጋበት ?

ለአንዲት ውብ ሙዚቃ ሀሳቤን ሰውቼ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

ለአንዲት መልካም ቅኔ ባርነት ገብቼ
ህሊናዬን፣ ቀልቤን፣ አካሌን ሰጥቼ፣
ለአንዲት ቅጽበት ብቻ !
የአምሮዬ መርከብ ከማዕበል አምልጣ
ከሕይወት ስንክሣር አምርራ ፈርጥጣ
በዕፁብ - ውበት ቅኝት እጅግ ተመስጣ
ሌላው ሌላው ነገር ባፍንጫዬ ይውጣ !

ደበበ ስይፉ ሐምሌ 5 ቀን 1942 ዓ.ም. በሲዳሞ፡ ይርጋለም ተወለደ። የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በይርጋለምና በአዲስ አበባ ኮከበ ጽባህ ትምህርት ቤቶች ተማረ። ከአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ከፍ ባለ ማዕረግ የመጀመሪያ ድግሪውን አገኘ። በእንግሊዘኛ ሥነ ጽሁፍ የማስተር ድግሪውን ተቀበለ። ከ1966 እስከ 1984 በረዳት ፕሮፌሰርነት አገለገለ። ለበርካታ ዓመታት የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኀበር ፕሬዜዳንት ሆኖ ሰራ። በቀድሞው ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ያልታተሙ መፃህፍት ገምጋሚም ነበር። ከ1985 ዓ.ም. ጅምሮ ለሰባት ዓመታት ታሞ ማቀቀ። ሚያዝያ 16 ቀን 1992 ዓ.ም. በተወለደ በሃምሳ ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። ሚያዝያ 17 ቀን 1992 ዓ.ም. ንፋስ ስልክ በሚገኘው የቅዱስ ዮሴፍ ቤተ ክርስቲያን መካነ መቃብር በድኑ አረፈ።

ከተማሪነቱ አንስቶ በርካታ ግጥሞች ጽፏል። «የብርሃን ፍቅር» የተሰኘ የመጀመሪያ የግጥም መድበሉን በ1980 ዓ.ም. በኩራዝ አሳታሚ ድርጅት አሳተመ። የብርሃን ፍቅር ሁለተኛ ክፍል የሆነውንና ፦ «ለራስ የተፃፈ ደብዳቤ» የተሰኘውን መድበሉን ደግሞ በ1992 ዓ.ም. በሜጋ አሳታሚ ድርጅት ታተመ። በተውኔቱ ዘርፍ «የቲያትር ጥበብ ከፀሐፊ ተውኔቱ አንፃር» የሚለው መጽሐፉ፣ «ሳይቋጠር የተፈታ» እና «ከባህር የወጣ ዓሣ» የተሰኙት ቲያትሮቹ ቢጠቀሱ ይበቃል…ጥናታዊ ፅሁፎቹም በርካታ ናቸው።

«አታልቅስ አትበሉኝ» ይላል ታላቁ መብረቅ፦ አታልቅስ አትበሉት - ግዴለም ይውጣለት … ይንፈቅፈቅ - ይንሰንሰቅ የልቡን አዳኝ ሆኖ ፍቅር ያድንለት - አምባ ጅግና ሆኖ ውበት ያድንለት…።

## አታልቅስ አትበሉኝ

አትሳቅስ በሉኝ
ግዴለም ከልክሉኝ፣
የፊቴን ፀዳል
አጠልሹት በከሰል፣
የግንባሬን ቆዳ
ስፉት በመደዳ፣
ጨጓራ አስመስሉት።
ግዴለም።
አትጫወት በሉኝ
ዘፈኔን ንጥቁኝ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

ግጼለም።
ብቻ ፤
አታልቅስ አትበሉኝ
አትጨህ አትበሉኝ ።

ከሰባት ዓመት በፊት ደበበ ሰይፉ እንዳረፈ ሰሞን ስሙን፦ በጋዜጣ፤ በመጽሔት፤ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ሲነሳ ሲወሳ ከርሚል። እስከዛሬም ይታወሳል። ዛሬም ሰባተኛ የሙት ዓመቱን እንዘክረዋለን። ይህን የምናደርገው ፕሮፌሰር ስለሆነ ፤ ገጣሚ ስለሆነ ፤ አንደበተ ርቱዕ ስለሆነ ፤ ፀሐፊ ተውኔት ስለሆነ ፤ ጠቢብ ስልሆነ ብቻ አይደለም ። በዛሬው ዘመን ስለሱ ተወሳ - አልተወሳ ምንም ቁም ነገር የለውም። ሳንታሮ ታኒካዋ ዕፎት ጆርጅ ጊሽ ጀር የተረጎመውን፦ "What the dead man left behind" የሚለውን ግጥም አስታውሶ ትካዜ ባሚሸው ዝምታ ማለፍም ይቻል ነበር። ነገር ግን ጋሽ ደበበ ሁሉንም «ልዩ» ነገር እንደነበር የማያውቁት እንዲያውቁት ያስፈልጋል።

ጋሽ ደበበ ሁሉንም «ልዩ» ነገር ነበር። ልዩ ፕሮፌሰር፤ ልዩ ባለቅኔና ገጣሚ፤ ልዩ ተናጋሪ (አራተር)፤ ልዩ ተፈላሳፊ፤ ልዩ ፀሕፊ ተውኔት፤ ልዩ ጠቢብ፤ ልይ ሩህሩህና ደግ፤ ልዩ «ቅዱስ» አማፂ፤ ልዩ ልዩ ነበር።

## ፍርሃት አዶከብሬ

ፍርሃት አዶከብሬ
አያ እናት አይምሬ
የቁም መቃብሬ
የቅዥት አገሬ።
ከሥጋ ከነብሴ ከደሜ ቆንጥሬ
ከአጥንቴ ሰንጥሬ፤
ምስህን ሰጥቼህ ላመልህ ገብሬ፤
ያው ነህ አንተገና
ልጓምህ አይላላ።
ትጋልበኛለህ በእሾህ በቆንጥር ላይ
ጨለማ እንደ ግራር በቅሎበት በሚታይ
　　አንዲት ዘሃ-ጮራ
　　　　በማትደፍርበት
እውነት - ፍቅር - ውበት
　　　　በተቀበሩበት።

ቅዱስ አማፂ ሆኖ ሳለ ከውስጡ አልነቀል ያለውን የፍርሃት ርዝራዥ በ«ፍርሃት አዶከብሬ» ውስጥ ያሳየናል። ካልፈራህ እንዴት ቅዱስ አማፂ ትሆናለህ? ትፈራለህ፤ ትደፍራለህ። ድፍረት በፍርሃትህ ልክ ነው። በፈራኸው መጠን ትደፍራለህ። የማትፈራ ከሆንክ፦ የማትደፍር ነህ። የማትደፍር ከሆንክ የማትደፈር ነህ፤ (ብዙ ጊዜ)። የማትፈራም የማትደፍርም ከሆንክ ደግሞ በድን ነህ። ቅዱስ አማፂነትህ የፍርሃትና የድፍረትህ ድምር ውጤት የሚሆንበት (አብላጫ) ጊዜ አለ።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

<u>የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም</u>

«ጋሼ ደበበ እንዴት ኮሚኒስት እንደሆነ» አንድ ሰው ሲያወጋ፡-

ያኔ ተማሪ ነበር አሉ።

ስታዲየም ዙሪያ አንድ ምግብ ቤት ገባ። እርቦታል። ምግብ አዘዘ። የመብል አምሮት የሠራው ምራቅ በአፉ ግጥም እያለ ትንሽ «አፋዊ» ኩሬ ይሰራል። ያዘዘው ምግብ እስኪቀርብለት በመጠባበቅ ላይ እያለ አንድ ሰው በዝግታ ወደ ውስጥ ገባ። ቡትቶ ለብሷል፤ ዓይኖቹ በደረቀ ፊቱ ውስጥ ተቀርቅረዋል። እንደራበው ያስታውቃል። ተያዩ። የዓይን ግጭቱ ቁም ነገር ያዘለ ከባድ ሃሳብ ሰራ። ያ ሰው ሊናገር ከሚችለው በላይ ለጋሽ ደበበ መልዕክቱ ደረሰው፦ «እርቦኛል ፤ በልተህ ሲተርፍህ እንድትሰጠኝ» ነው ያሉት የሰውየው ዓይኖች። ጋሽ ደበበ ግን ከዚህ በላይ ገባው።

አምሮት በሰራው ምራቅ ግጥም ያለ አፉ ክው አለ። የታዘዘው ምግብ እየመጣ ነበር። እፊቱ ተቀመጠ። መብሉን አየው ጋሽ ደበበ። ከመቀመጫው ተነሳ። አነሳው ምግቡን። ለሰውየው ሰጠው። መስጠት ጀምሮ መስጠቱ ከማብቃቱ በፊት በአንድ ጊዜ ሁለት ነገሮች ሆኑ...ከውጭ ግር ያሉ ቡትቶ የለበሰው ሰውዬ ጉስቁል አጃቢዎች መሻማት ጀመሩ። ይሄ አንዱ ነገር ነው። የምግብ ቤቱ ባለቤት ባለቡትቶውን ሰውዬ መቀጥቀጥ ጀመሩ፤ ይሄ ደግሞ ሌላው ነገር ነው። ምግቡ ተደፋ። ጉስቋላው ሰውዬ ደማ። ምግቡ፤ ደሙ፤ አሸዋው፤ አፈሩ፤ ጠጠሩ ሺህ ዓመት እዚያ ቦታ የቆመ ያህል ተሰማው። ተንቀሳቀሰ። ወዴት እንደሚሄድ ሳያውቅ መራመድ ጀመረ።

ከዚያን ቅፅበት ጅምሮ በኮሚኒዝም ተጠመቀ።

ታላቁ መብረቅ ከሰባት ዓመት በፊት አመለጠ።

ትናንት ከኛ ጋር ነበር፤ ዛሬ የለም። የጊዜ ጉዳይ ነው። በጊዜ ላይ ሲፈላሰፍ የቋጠራቸው ስንኞች ስለስብዕናው የሚሰጡት ስዕል አለ። «ጊዜ በረርክ በረርክ» እና «ዘመዴን ስስመው» ይለናል። እነሆ፦

## ዘመዴን ስስመው

ዘመዴን ስስመው
ጉንጩ ቢሻክረው
እኔንም ሻከረኝ
ዕድሜ መለስለሱ ማብቃቱ ታወቀኝ።

## ጊዜ በረርክ በረርክ

ጊዜ በረርክ በረርክ
ጊዜ በረርክ በረርክ
ግና ምን አተረፍክ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

ግና ምን አጎደልክ?
ሞትን አላሸነፍክ
ሕይወትን አልገደልክ።

ጋሽ ደበበ ሞቷል። ታላቁ መብረቅ አልፎአል። ወይም አርፏል። ትዝታውና ሥራው ከእኛ ጋር እየኖረ፣ ጥልቅ ሥራው ከትውልድ ትውልድ እየተዘከረ ህያው እንደሆነ ይቀጥላል። «የክረምት ማገዶች» በሚለው ግጥሙ ወደ ሌላው እንሸጋገር።

## የክረምት ማገዶች

እንዲህ ተጫጭሰን
እንዲህ ተጨናብሰን፣
ውሀ እንዳለዘዘን
ከውሀ ተዋግተን…ተዋግተን…ተዋግተን
ውሀን አሸንፈን፣

እሳትን ፀንሰን
እሳትን አምጠን…አምጠን…አምጠን
እሳትንም ወልደን፣
እሳትንም ሁነን፣

/የክረምት ማገዶች/

ካጨለጨልንለት የድሃውን ጎጆ፣ ቀጫ ከል ጭራሮ
ካበሰልንለት ዘንድ፣ የአርሶ አደሩን ንፍሮ
የሰርቶ አደሩን ሕዝብ፣ ለሰስ ያለ ሽሮ፣

ታሪክ ይዘምረው የኛን እንጉርጉሮ።
ዘመን ይመስክረው፣ የኛን ውጣውረድ፡
    የእንግልት ኖሮ።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ
ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

# ክፍል አንድ

## ሀያሲ፤ ገጣሚና የስነጽሑፍ ተመራማሪ

የኮከብ ክብር ብርሃኑ ነው። የኮከብ ኮኮብነትም በጨለማ ነው። አንዱ ኮከብ ከሌላው በጸዳሉ ይበልጣል። ለዚህም ነው የንጋት ኮኮብ፤... እያልን የምንለያቸው። ካንዱ ኮከብ ሌላው ኮኮብ በክብር ይበልጣልና።

ሚያዝያ 16, 1992 ዓ.ም. አንድ ኮከብ አጣን። ብርሃን አፍቃሪ ብርሃን አጣን። ይህ ቀን ዛሬ ስባት ዓመት ሞላው። ይህ ቀን የሐዘን ቀናችን ነው። ለምን?

ደበበ ሰይፉ ሐምሌ 5 ቀን 1942 ዓ.ም. በይርጋለም ከተማ ተወለደ፤ እድገቱ ግን አዲስ አበባ ሆነ። የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ ወደ አዲስ አበባ መጣ። እዚህም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱን በቀድሞው ቀ.ኃ.ሥ. በአሁኑ ኮከበ ጽባህ ትምህርት ቤት አጠናቋል። ወደ ዩንቨርስቲም ከገባ በኃላ በአካውንቲንግ ዲፓርትመንት አንድ መንፈቅ ተምሮ የህይወቱ መግለጫ፤ የኑሮው ጎዳና አልነበረምና ወደ ኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ገባ። የፈለገውን አገኘው። ከዚያም በ1965 ዓ.ም. በማአዕረግ ከተመረቀ በኋላ እስከ 1985 ዓ.ም. ድረስ ለ20 ዓመታት በዩንቨርስቲው በመምህርነት አገልግሏል። በመሀል የማስተር ድግሪውን በእንግሊዘኛ ሥነጽሑፍ በ4.00 ነጥብ አጠናቋል፤ ሁሉንም ሀ በማግኘት። በሥራቸውም ጥናትና ምርምሮች የረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ አግኝቷል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

## የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

የሥነ ጽሑፍ መምህሩ ደበበ ሀያሲ ነበር። የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ በሆነ አቅጣጫ እንዲንቀሳቀስ አድርጓል። በኢትዮጵያ ቲያትር፤ በኢትዮጵያ ሥነግጥም፤ በኢትዮጵያ ልቦለዶች ላይ ብዙ ጥናታዊ ጽሑፎችን አውጥቷል። አበይት ያማርኛ ገጣምያንን ሥራዎች አጥንቷል... መነሻ ጥናት። የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ ቃል ያጣላቸውን ቃል በመፍጠር ከነ ዮሐንስ አድማሱ ቀጥሎ የሚጠቀስም ነው፤ ደበበ። ዛሬ የሥነጽሑፍ አፍቃሪው ሁሉ አፍመፍቻ የሆነችው መቼት (setting) የደበበ ፍጡር ናት። ሌሎችም ስያሜ ቃላት። የቲያትር ጥበባትን ከቀድሞው በላቀና በረቀቀ መንገድ ለባለሙያውም ለአፍቃሪውም እንዲስማማ አድርጎ የፃፋትና በ1973 ዓ.ም. የታተመችው «የቲያትር ጥበባት ከጸሐፌ ተውኔቱ አንፃር» ግንባር ቀደም ስራው ናት።

ደበበ ጸሐፊ ተወኔት ነበር። ብዙ ተውኔቶችን ጽፏል፤ ለመድረክም አብቅቷል። «ሳይቋጠር ሲተረተር»፤ «እነሱ እነሷ»፤ «ከባህር የወጣ ዓሣ»፤ «የህፃን ሽማግሌ»...። የተውኔቶቹ ልዩ ባህርይ እምቅነታቸው ነው፤ እንደግጥሞቹ። «ከባህር የወጣ ዓሣ» የሚያስፈራራን ሀቅ የምናይበት፤ የሚያስፈራራን እውነት የምናይበት፤ የሚያስፈራራን እውነት የምንሰማበት፤ ሰበናችንን ወደ መመርመር የምንመለስበት ነው።

ደበበ ከፍ ያለ ማዕረግ የሚሰጠው ባለቅኔ ነበር፤ በግጥሞቹ። ግጥሞቹ ማህበራዊ ጉዳዮችን
ያነሳሉ። ረሀብን፤ ጦርነትን፡ ድቀትን፤ ትንሳኤን፤...ሁለንተናዊ የሆኑትንም ያነሳል ፍቅርን፤
ጥላቻን፤ ጓደኝነትን፤ ቅናተን፤...ሁሉንም ቢያነሳም ጽልመታዊ አይደለም። የመዝሙሩ ሁሉ
መጨረሻ ብርሃን ነው፤ ተስፋ። በፀፀት፤ በልቅሶ፤ በድቀት ህይወትን ትቢያ የሚያደርግ ተስፋቢስነት
የተሞላበት ድምፀት የለውም። ባለ ብሩህ ተስፋነቱ "ተስፋ መቁረጥን" ተስፋ እስከማድረግ የዘለቀ
ነው። የግጥሞቹን ቅርጽ ያየን እንደሆነ እንደቀድሞዎቹ የግዕዝ እውቀቱ የመጠቀ ባይሆንም
በዩንቨርስቲና በግሉ ባገኘው እውቀት የግዕዝ ቃላት ጌታ ነው። የአማርኛ ቃላትም ጌታ ነው።
"ህያው መዝገበ ቃላት" የሚሉትም ነበሩ። ቃላትን አክብሮ ልዩ ማዕረግ ይሰጣቸዋል።
ልቅሶ፤ ሳቅ፤ ገደል ማሚቶ፤ አዋይ፤ ፀሐይ፤ ጨረቃ፤... የራሱን ፍቺ ሰጥቶ የሀሳብ ጎተራ
አድርጓቸዋል። የገደል ማሚቶን የህዝብ ብሶት አዳማጭ ያደርጋታል፤ በኋላም ምስክር። አዎይን
የእጦትና የማግኘት ተምሳሌት አድርጎ፤ ፀሐይን የህይወት የእውነትም፤ ጨረቃን የተስፋ፡
የውበትም፤.. ልዩ ኃይል፤ ልዩ ፍቺ ይሰጣቸዋል፤ ለቃላት።

አዋይን ሰማኋት ስታለቅስ በይፋ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ
ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

ከጎጆሽ ስትወጣ ትቢያዋን አራግፋ።

…

የገደል ማሚቶ መጣች፡ በዘመን ጭራ ታስራ።
የአእላፍ ሙታን ድምፅ፡ ቋጥራ።
አደራ።

የግጥሙን የወረቀት ላይ ቅርፅ የግጥሙ ሀሳብ ተሸካሚ እያደረገም ያሳየናል።
ብሉይና ሐዲስን
በዘይቤነት በመጠቀም የግጥሞቹን ሀሳብ ያሰፋል።…ግጥሞቹ የባለቅኔ ናቸው።
እስካሁን ሁለት
የግጥም መድበሎች ብቻ ናቸው የታተሙለት፤ አንዱ በ1981 ዓ.ም. ሌላው በ1992
.ም.የብርሃን
ፍቅሮች። በእንግሊዘኛ አንድ መድበል የሚሆኑ ግጥሞች አሉት። ሥነቃላችንን
ተጠቅሞ ግጥሙን
ያብራራል፤ ያፋፋል። «መስከረም» «በተረት ላሰላስልን» «አጸለሌን»…በሌሎቹም
ግጥሞቹ ውስጥ
ሥነቃልን እየተጠቀመ ሊለው የሚሻውን ብሎባቸዋል።

ደበበ መምህር ነበር። ብዙ ተማሪዎችን አፍርቷል። የኢትዮጵያ የቋንቋዎችና
ሥነጽሑፍ
ዲፓርትመንትና የቲያትር ዲፓርትመንትን የተሻለ መልክ እንዲይዝ አድርጓል።
በመምህርነቱም በተማሪዎቹ የተወደደ፤ በመምህራን ጓደኞቹም የተከበረ ነበር።
በዛሬው የሥነጽሑፍ
መድረክ የሚገኙት ብዙዎቹ የሱ ተማሪዎች የነበሩ ናቸው።

ደበበ በ1970ዎቹ መጨረሻና በ1980ዎቹ መጀመሪያ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር
ሊቀመንበር
ነበር። በዚህ ወቅት ነው ፈዞ የነበረውን ማህበር እንደማንቀሳቀስ አድርጎት
የነበረው። በየወቅቱ
በየቦታው በማህበሩ የተዘጋጁ ስብሰባዎች ይካሄዱ ነበር። አንድ ሆና ቀረች እንጂ
የምታጓጓዋን
የሥነጽሑፍ መጽሔትም የታተመችው በሱ ሊቀመንበርነት ጊዜ ነው፤ «ብሌን»
በዚያው ወቅት
የደራሲያን ማኅበር «እነሆ» የተሰኘ የአጫጭር ልቦለዶች መድበልም አሳትሞ
ነበር። ሁሉም
በደበበ ከበሽታ መያዝ ጋር ከሰመ። የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ በረጅም ልቦለድም፤
በግጥምም እመር
ያለብት ወቅት ላይ በባህል ሚኒስቴር ውስጥም፤ በኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ቦርድ
ውስጥም ሆኖ
ሰርቷል። በአጠቃላይ የታተሙት ሥራዎቹ አራት ናቸው 1. የቲያትር ጥበባት
ከጸሐፊ ተውኔቱ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

አንፃር 2. ማርክሲዝምና የቋንቋ ችግሮች 3.የብርሃን ፍቅር ቅጽ 1 እና 4. የብርሃን ፍቅር ቅጽ 2. ከነዚህ በተጨማሪም በርካታ ጽሑፎችና ብዙ የትርጉም ሥራዎች አሉት።

ደበበ በአበባው የቀረ ነው። በወጣትነቱ ያካበተውን ሁሉ መልክ መልክ አሲዞ በእርጅናው ሳይሰጠን
አመለጠን፤ ተቀማን። ያንን ያማረ፤ የተዋበ፤ የተሻለ፤ ደግና መልካም ብዕሩን እንደያዘ
ወደ መቃብር ወረደ። ደበበ ሀብተ ሃሳብና ሀብተ ቅኔን አስተባብሮ በድካሙ የያዘ ነበር። እውነትን፤
ውበትን፤ ህይወትን ፍለጋ በራሱ ውስጥ እንደባሰነ አረፈ፤ እያንጎራጎረ ተሰናበተ።

ተይው እንተወው፤
የዘመን ቃፊሩን ማለፍ አልቻልንና
ይህ ዓለም ጥበቱ አልመጠነንና
ተይው እንተወው…
ውጥኑ ግብ ይሁን
ጅማሪው ፍጻሜ
ቅጽበቷ ሙሉ ዕድሜሽ
ወቅቷ ዘላለሜ።

በውጥንና በጅምሩ ቀረ። ብዙ ሰጥቶናል፤ ግን ከሱ ልናገኝ ከሚገባው ውስጥ ብዙ በጣም ብዙ
ቀርቶብናል።

ደበበ የፈራውን ሞት ደፍሮታል። የደፈረውን ሞት አቅፎታል። እንዲህ እያለ፤

ማራድ ማስፈራቱ በል የታል፤ የሞት ምንነቱ?
በንጹህ ልቦና ብርታት፤ በቤተሰብ አለኝታ እምነት
ይዘልቋል ለካስ፤ እሚፈራውን ዳገት…
አቀበት።

ዛሬ የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ አንድ ለጋ ብዕር አጣ፤ ነጥፎ አይደለም ታጥፎ ነው። ዛሬ የኢትዮጵያ
ሥነ ጽሑፍ የዋህ ሀሳብ አጣ፤ ከፍቶ አይደለም በኖ ተኖ እንጂ። ዛሬ ብዙዎቻችን ካወቅነው ብዙ
ነገር አጣን። ካላወቅንም እሰየው ከእንጉርጉሮና ከፀፀት ተረፍን። ደበበ የደራሲ "ሞት" አይደለም
የሞተው፤ የከያኒ። የደራሲ ሞቱ ብዕሩ የነጠፈ፤ ሀሳቡ ያረጠ እለት ነው። ደበበ ብዕሩ እንዳጋተ
የሚያጣባው ጠፍቶ ባክኖ ቀረ። የሚቆጨውም የሚያስደስተውም ይሄ ነው። አለዚያማ እንደራሱ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

እንደ ደበበ አንጉርጉሯችን።

የከያኒው ዓይኑ
ምናቡ ብሌኑ
ጠየምየም እያለ
ጭስ እየመሰለ
መሄድ ከጀመረ
ያ ነው ምልክቱ
የግንዘት የሞቱ።

የሚል ይሆናል። ግን አልሆነም። አሁን የፀፀት ሮሮ ነው፤ ወይኔ፤ አዬ ጉድ፤ ትንሽ በቆየልን
የማለት፤ የመናፈቅ ነው፤ ባልሞተ ማለት።

ደበበ ግጥሞቹ ሕዝባዊ ናቸው። ለቅሶው ስለ ወገን ነው። የብዕሩ አርማ፤ የሀሳቡ ባንዲራ ሰው
ነው። ናፍቆቱም።
ይኖር ይሆን አርማ፤ ይኖር ይሆን ውይ ባንዲራ፤
ሰውን የመሰለ ቀለም ያለው ሰውን የመሰለ አሻራ፤
እማይወድቅ፤ እማይታጠፍ ሰንደቅ
እማይከስም፤ እማይዳፈን ደመራ?…
የሚል ይሆናል።

ሀብትን በማካበት ጊዜውን ያላጠፋው ደበበ ከእውቀቱና ከብዕሩ በቀር አንዳች አልነበረውም፤
እንዲኖረውም አልጣረም። የጣረውስ የደከመውስ፤

አይደለም ለክብረት ለንዋይ ተዳምሮ
አይደለም ለሹመት ተጫፍሮ ኑሮ
አይደለም ለዝና ለጠፊ ውሎ አድሮ፤…
ለትሁት ሕይወት ነው፤ እኔ መሯሯጤ
በዘልማድ መንገድ ጉዞ አለመምረጤ፤
ደቂቀ ብርሃንን…
ውበት ፍቅር እውነትን
ለመገላገል ነው፤ የዘወትር ምጤ።
በማለት ነበር።
ደህና፡ ደበበ ከመቃብር ባሻገር በብዙዎቻችን ልብ ውስጥ ከነብርሃንህ አለህ።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ
ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

# ክፍል ሁለት

## ከሥነ - ጽሁፍ ሰማይ ላይ ደማቁ ኮከብ ወደቀ

ገጣሚ፣ ደራሲ፣ ተርጓሚና የሥነጽሑፍ ተመራማሪው ደበበ ሰይፉ ሚያዝያ 16 ቀን 1992 ዓ.ም.
በተወለደ 50 ዓመቱ ሕያው ሥራዎቹን ትቶልን አልፎዋል።

ደበበን ለማወቅ ብዙ ከመድከም ግጥሞቹን ልብ ብሎ ማጤን ይበቃል። ከአንዱ ታላቅ ተራራ ላይ
ፏፏ…ዷዷ… እንደሚል ፏፏቴ ውስጥ የሚንፏለል የሕይወት ውሃ ነው።

ደበበ ዝምተኛ ባይተዋር ነገር ቶሎ ሆዱ የሚገባ የገጣሚ ነፍሱ የንስር ዓይን ያለው ነው። የደበበ
ግጥሞች  እየተሳቡ እየተተረተሩ የሕይወት ድር ያደራሉ። ምጸታቸው ይሰማሃል፡ ኅዘኑ ይገባሃል፡
ፍቅሩን ታፈቅረዋለህ፡ እጦቱ ያሳጣሃል፡ እንዲ ነው መንፈስን ገዝቶ ስሜትህን ኮርኩሮ ራስህን



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

የሚያሳይ የጠራ የሕይወት መስተዋት ነው።

ደበበ ግጥሞቹ በሁለት እግራቸው ቆመው ይሄዳሉ፡ የውስጥ ባዶነት የተሰፉን ብሩህነትና ሙጥኝ
ባይነት ባጭሩ በተባ ብዕሩ አሳምሮ ያየ ግሁዝን ከሕያዋን ያናጸረ የሚናገረውን ብቻ
ሳይሆን የማይናገረውን ጭምር ያናገረ በስራው ለሀገር መኩሪያ የሆነ እውቅ ገጣሚ ነው። የሂስ
ዓይኑ በስሜት ያልተዳከመ በብሶትና በእውነት ላይ የተመሠረተ ነው። ትርጉሙን የወጥ ሥራን
ያህል ከሕዝቡ ሕይወት ጋር የሚያስማማበት የተለየ ተሰጥዎ እንዳለው አስመስክሯል።

ደበበን በሥጋ ዓይን እንግለጸው ካልን ሲዳሞ ይርጋለም በወርሃ ሐምሌ የአቦ ዕለት በ1945
ዓ.ም. ከእናቱ ከወ/ሮ የማርያም ወርቅ አስፋውና ከአባቱ ከአቶ ሰይፉ አንተንይስጠኝ ተወልዶ
ይህቺን ዓለም እሪ ብሎ በጩኸቱ አደፍርሷታል። ዋይታ የማያቆምባት መከራ ያልተለያት መሆኑን
ከፍ ሲል በገሃድ የሰውን ልጅ ማኅበራዊ አመሳሶ አጠንክሮ ተቃውሟል።

ደበበ «ይርጋለም ዋ የልጅነቴ ቀለም» ባላት የእትብቱ መቀበሪያ የሱነቱ አሻራ ማሳያ ዋን
ይርጋለም በስስት በቁጭት በሀዘን ገልጿታል። በየብርሃን ፍቅር ይርጋለም አንዴ ብቻ ሳይሆ ሁለት
ሶስቴ በየቦታው አምራ ደምቃ ወጥታለች። እዚያ ቀዬው ነው በራስ ደስታ ት/ቤት የመጀመሪያ
ትምህርቱን የጨረሰው።

ደበበ በትላንቱዋ አዲስ አበባ የ2ኛ ደረጃ ትምህርቱን በኮከበ ጽባህ ት/ቤት በ1959 ዓ.ም. ፊጽሞ
በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ በትጉህ የሥራ ውጤቱ የመጀመሪያ ዲግሪውን ብ1965 ዓ.ም. በማዕረግ
ያገኘ ሲሆን ዕድሜውን ባሳለፈበት የሥነጽሑፍ ሥራው የሁለተኛ ዲግሪውን በ1972 ዓ.ም.
አግኝቶዋል።

ዛሬ የደበበ ግጥም አሻራ የእሱ የማስተማር ውጤት የፈጠራቸው በርካታ የሥነጽሁፍ ባለሙያዎች
ተፈጥረዋል። ከ1966 እስከ 1985 ድረስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ እንዲሁም በቴያትር
ጥበባት ክፍል በመምህርነትና በኃላፊነት አገልግሏል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

የብርሃን ፍቅር ቅጽ አንድ እና ሁለት የግጥም መጽሐፎቹ እንደ ጽጌሬዳ ብዕር ባሉ የ17
ገጣሚያን የስብስብ ሥራዎች ውስጥ እና በብሌን የደራሲያን መጽሔትና በሌሎችም ቦታዎች
ግጥሞች ለንባብ በቅተዋል። በዩንቨርስቲ ላሉ ተማሪዎች ለመማሪያነት የሚያገለግሉ በዋቢነት
የሚጠቀሱ የተለያዩ ግጥሞችና የጥናት ጽሑፎች አበርክተዋል።

የቲያትር ጥበብ ከጸሐፊ ተውኔቱ አንጻር ለተውኔት ባለሙያዎች ለተደራሲያን ለቲያትር
ደራሲያንና ሐያሲያን ላቅ ያለ አስተዋጽዎ በማበርከት ላይ ያለ መጽሐፍ ጽፏል። ደበበ የቲያትር
ደራሲ ነው። እንደ ከባሕር የወጣ ዓሣ፤ እናትና ለጆቿ የሚሉት ከወጥ የቲያትር ሥራዎቹ መሃከል
የሚጠቅሱ ሲሆኑ በትርጉም በተደጋጋሚ በቴሌቪዥን የቀረበው «አንድ ክፍተት» የደበበን
ለቲያትር ድርሰት በሳል ተርጓሚነት ማጣቀሻ ይሆናል።

ደበበ ፍቅር እትሞቹ ብዙ የኑሮ ውጣ ውረዶችን፤ የሀገሪቷን መልካ ምድራዊና ተፈጥሯዊ
ቦታዎችን፤ የአስተዳደርና የማኅበራዊ ፍትህ መዛባትን፤ የሰውን ልጅ ሕልምና ምኞትን በተባ ብዕሩ
አጉልቶ አሳይቶናል።

ነብይ መኮንን «ከዓለም አንድ ጣት» ባለው ግጥሙ እንዳለው፤ ከዓለም ላይ አንድ ጣት
መቀነሱን የደበበን ሞት ሲሰማ ብዕሩን አንስቶ «ሕቅ» ያለው ያለ ነገር አይደለም። አዋቂ በላምባ
እየተፈለገ በሚገለልበት፤ ተንቆ በሚተፋበት፤ እውቀቱ ሳይጠገብ ወግድ በሚባልበት ዓለም በተለይ
በእኛው ሀገር አንድ አይደለም አምስት ጣት አጥተናል።

ደበበ ከማስተማር ሥራው ሳይወድ የተገፋ፤ ዘመን በወለዳቸው የፖለቲካ ሹም ከያኒያን ያልተገራና
ያልታረመ አንደበት የተተፋበት መሆኑን ራሱም፡

«ለምን ሞተ ቢሉ
ንገሩ ለሁሉ
ሳትደብቁ ከቶ
“ከዘመን ተኳርፎ
ከዘመን ተጣልቶ»”
ማለቱም ያለነገር አይደለም።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

## <u>የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም</u>

ደበበ እንደ ሶቅራጥስ አለማወቄን ማወቄ ያስደስተኛል ማለቱን በግጥሞቹ ያሳይሃል። መኮፈስን
አወቅሁ ብሎ በሕዝብ ላይ መጀነንን ቦታ እንደማይሰጠው በተባ ብዕሩ፡ በበሳል ክህሎቱ አጉልቶ
ያሳየናል፤ በሒስ ዓይን ያመላክተዋል። «ድንቄም መምህር» «ያባትህ ልጅ» እና ሌሎችም
ይጠቀሳሉ።

ደበበ ሳናከብረው፡ ተገቢውን ቦታውን ሳንሰጠው፡ በፖልቲካ አግቦ፡ በዘመን አመጣሾች ትዕዛዝ
ታግሎ እንደልብ ልናወጋው ያልቻልን፡ የፍላጎቱን ያህል ያላስተማረን፡ ያሰበውን ያህል ሳይጽፍ
ያደናቀፍነው በሳልና ላቅ ያለ ችሎታ ያለው ዘርፈ ብዙ የሥነጽሑፍ ሰው ነው።

ደበበ ሕዝባዊ ገጣሚ ነው። ከትላንት እስከ ዛሬ «በክረምት ማገዶች»፤ «በአክሱም ጫፍ
አቁማዳ»፤ «እማማ እማማዬ»ና በሌሎችም የሚያለቅሰው ለሕዝብ ነው። ገጣሚ ዛሬ ላይ ቆሞ
ነገን ጭምር እጣውንና እጣችንን የሚያይ መሆኑን ግጥሞቹ ጉልህ ምስክር ናቸው።

ደበበን እንዲገለል ያደረጉ፡ ሊያፍኑት የቃጡ፡ ስሜቱን የጎዱ፡ ያለ በደሉ በበቀል ካራ ሕሊናውን
የወጉም፡ ሕያው ሥራዎቹን ሊያደበዝዙ ሊገንዙ አይችሉም፤ ገጣሚ አይሞትም ሥራው መጠሪያና
ሐውልቱ ነው። ልክ ሰለሞን ደሬሳ ቢጠየቅ «ዘላለምሽ ዘላለሜ ዘላለምነቱ» እንደሚለው ደበበም
የግጥሞቹና የሌሎች ድርሰቶቹ ዘላለማዊነት ለሱም ዘላለማዊነትን ያቀዳጁለታል፡ ሞትን
ያሸንፉለታል።

ሰሪውና ምጥቁ፡ ግዙፉ ዓለም ጣራ የሆነው ግዙፉ የሥነጽሑፍ ሰማይ እንደ ፀሐይ የሚያበሩ ሌት
ከጨረቃ ጋር ደምቀው የሚያፈኩ፡ የሚንተገተጉ የእውነት፡ የውበት የሕይወት ደማቅ ክዋክብት
መሀከል ደበበ አንዱ ነው። ዛሬ አሻቅበን ያን የሥነጽሑፍ ሰማይ ብናይ ደማቁ ኮከብ ወድቋል።
የኮከቡ ብርሃን ነፀብራቅ በብርሃኑ የምናየውን ሕያው ጥበብ አጎንብሰን መጽሐፎቹ ውስጥ መፈለግ
ነው። ቀና ብለን ከወትሮው ቦታ አናገኘውምና።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

## ክፍል ሦስት

## ሐዘንህ አመመን

«…ሰዊራ-አሸዊራ-ኑሸዊራ-አቄራ-ነቂራ
አዝቢራ-አዥበርባሪ-አጽቢራ-አጽበርቢራ
ሐሊል ላሓል ቃኢል ባኢል ናኢል
ባባባላላላፊፊፊዳዳዳ-ሀሀሀ(ሀ-ሀ-ሀ)…»



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

ሰላም ቤቶች…እንዲህ ያለ ቋንቋ ሰምታችሁ ላታውቁ ትችላላችሁ፡ ደግሞም አልሰማችሁም። እሱ
ግን ሰምቷል። ሰምቶም ታዝቧል፡ ታዝቦም ተቆጥቷል። እሱ ሲቆጣ ብዕሩን ይመዛል። ከቃላት ጋር
ይጫወታል፡ በሰላቅ ይሸነቁጣል። ማንነትን ያጠያይቃል። ማነህ አንተ ይላል።

የተማረና ዘመናዊ ነኝ የሚለው ወገን ማንነቱን እሱነቱን ዘንግቶ በተውሶ የባህር ማዶ ቋንቋ
ሲፏንን የሚታየውን ወይም እንደራሱ አገላለጽ «አንቺ ልጅ ኩሪባቸው፤ በእንግሊዘኛ
አናግሪአቸው» የሚለውን ፈሊጥ የፈጠሩ ወገኖችን ደበበ በቁጣው በትር መቀጥቀጥ ያልፈራ ነው።
እነሆ ከዚሁ ግጥም ሌላ ቅንጫቢ፡

«…አሁን እንዳተ ማን ሊመጣ
አባቱን መስሎ የወጣ?
እንዳንተም የአባቱ ልጅ የለ
ጥበብን አቅፎ የገደለ
አወፍሮ ያሰለለ፡
አንድም አንተን መሳይ-አባቱን መሳይ የለ።
ራሱ በማይፈታው እንቆቅልሽ፡ ተረብ የድግምት ወጀቦ
ፈውስ እያለ ሲያደባይ፡ የስንቱን ቀልብ ስልቦ
አንተም የመዝለፊያ ልጅ ዛቢያ
ዘመናይ ደብተራ ዐባይ
ተጠበብኩ ስትል ጠበብክ
ዐወቅሁ ስትል ደነቆርክ
መቅረዝ ሲሉህ-እንቅቡም አንተው ሆንክ።…»

ይህን ግጥም የፃፈው በ1968 ዓ.ም. ነው። ርዕሱን «ያባትህ ልጅ» ብሎታል። ይህ ግጥም
የምሁራን ሀገርተኝነትና ሕዝባዊነት የሚያጠያይቅበት፡ የማንነት መለያውን መጣሉን እያወሳ
ያንጎራጎረበት የፀፀት ድምጽ ነው። በሌላ ገጹ ደግሞ እንደራሱ አባባል «የራሴ ግንዛቤ የተሃድሶ
ለውጥ መዝሙር» ነው ይላል።

ይህን የሚለው እውቁ ገጣሚና የዩንቨርስቲ መምህር የነበረው ደበበ ሰይፉ ነው። የዛሬ ሰባት
ዓመት ሚያዝያ 16፤ 1992 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። የዕድሜውን አብዛኛው በአዲስ
አበባ ዩንቨርስቲ በመምህርነት ያሳለፈው ደበበ ሰይፉ በዚያና በዚህ ትውልድ ውስጥ ትቶ ያለፈው
ህያው ታሪክ ግን ዛሬም አለ። ነገም ይኖራል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

ደበበ የወጣለት ምሁር ነው። ምሁር ደግሞ እውቀቱን ለሀገሩ እድገት የሚያውል፡
የሚተጋና
የሚጥር የዚች ሀገር ህዝቦች ሲበደሉ፡ ሲገፉ፦ ስለ ህዝብ ፍቅር ሲል እራሱን
አሳልፎ ሰጥቶ፡
ስህተትን ማረም የሚችል፡ የማይፈራ፡ ለራሱ የማይሳሳ፡ መሆን አለበት የሚል፡
ህያው እምነት
የነበረው ነው። ስለዚህም ነው ብጤዎቹን ምሁራን «ጎመን በጤና» ብለው እጃቸውን
በአፋቸው
አድርገው ግፍና በደሉን በአርምሞ ሲመለከቱት እሱ ብዕሩን መዞ እንዲህ
የሸነቆጣቸው።

## ጥሬ ጨው

መስለውኝ ነበረ ፡
የበቁ የነቁ
ያወቁ የረቀቁ
የሰው ፍጡሮች ፡
ለካ እነሱ ናቸው ፡
ጥሬ ጨው..ጥሬ ጨው
ጥሬ ጨዋዎች ፡
መፈጨት-መሰለቅ-መደለዝ-መወቀጥ-
መታሸት-መቀየጥ
ገና እሚቀራቸው ፡
"እኔ የለሁበትም !"
ዘወትር ቋንቋቸው ።

ደበበ ሰይፉ ይህን ጥሬ ጨው የተሰኘ ግጥሙን የፃፈው በ1971 ዓ.ም. ላይ ሲሆን ማነጣጠሪያዎቹም ገለልተኛ ጨዋ ምሁራኖች መሆናቸውን በ1980 ዓ.ም. በአሳተመው የብርሃን ፍቅር የተሰኘው የግጥም መድበሉ ላይ አስፍሮታል። በርግጥም ደበበ ሰይፉ ለሀገር ልማትና እድገት የሚጥርና የሚተጋ ብቻ ሳይሆን ለእድገት ለአዲስ ሕይወት መጎርሻት ለሚጥሩ ሁሉ ልዩ ፍቅር እንደነበረው በዚህ በተከታዩ «በትን ያሻራህን ዘር» በሚለው ግጥሙ ውስጥ የፃፈው ሲሆን የምኞት ሱስ ስለሌለባቸው ለሀገር ልማትና እድገት የትምና መቼም ቀና ደፋ ለሚሉ ወገኖች ማስታውሻ ትሁናቸው ብሏል።

## በትን ያሻራህን ዘር

በጓጥ በስርጓጉጡ
በማጥ በድጡ
እንደ ተንጋለልክ-እንደ ዘመምክ
ትንፋሽህን እንደ ቋጠርክ
ልል ቀበቶህን እንዳጠበክ ፤
የተልኮህን አባዜ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

## የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ
## ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

የሕይወትህን ቃለ-ኑዛዜ
    ወርውር !
    የእጅህን ዘገር ።
በትን !
    ያሻራህን ዘር ።
ይዘሽው እንዳትቀበር ።

ደበበ ሰይፉ ስለሀገርና ወገን የሚሰማው ስሜት እጅግ ጠሊቅና ምጡቅ ነበር። በተለይ ደግሞ ሰለምሁራንና ስለ ሀገራቸው ያላቸውን ናፈቆት በመሳጭ ቃላት ነበር የገለጻቸው…በሐዘንሽ አመመኝ ግጥሙ ስለዚሁ ግጥም እንዲህ ብሎ ነበር።

«ሐዘንሽ አመመኝ፡ እንደ እማማ እማማዬ ሁሉ ከተማሪው ትውልድ መሃል በስጋም በመንፈስም ከሀገሩ እርቆ የነበረው ወገን የሚሰማው የቅሬታ እንጉርጉሮ ነው፡ የብክነት ዓይነተኛው ተገፎበት እራሱንና ሀገሩን ማተኮር ሲጀምር ከውስጡ የሚኮሰኩስ የነሱ ጩኸት ነው። ናፍቆት የፀፀት እሮሮ በሌላው በኩል ግን በእሱና በእሱነቱ ማለትም በሀገሩ መሃል የቆመውን ማንኛውንም ገደል አፈራርሶ የእሱነቱን መለያ የመፈለግና የማግኘት ቁርጥነት የሚሰማበት የተስፋው መዝሙር ነው።

እርግጥ ነው ሐዘንሽ እመመኝ እጅግ አያሌ ኢትዮጵያውያን በረሃብ በሚረግፉበት ወቅት የተፃፈ እንደመሆኑ ከሌላኛው ግጥም ይበልጥ ስሜትን ሊጫን ይችላል። እንዲያም ሆኖ ብስራት ፍፁም የተለየው አይደለም። ውጋገን፡ ቀቢፀ ተስፋ ያደቀቀው ትውልድ ድምፁም አይደለም። ከቶም…

እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉትን ስሜቶች። በሌጣው ብራና ላይ በቀለሙ ያለ ድካም የሚዘራው ደበበ «በሐዘንሽ አመመኝ» ግጥሙ ተስፋውን ምኞትና ራኢዮን እንደሚከተለው ነበር የከተበው።

አላውቅልሽ ብዬ አታውቂልኝ ብዬ
እምነትሽን ጥዬ ፍቅርሽን ገድዬ
አኩርፌሽ ስቀመጥ ያው እንደ ባላንጣ
ይኸው ነጭ ማተብሽ ሊያስታርቀን መጣ፤
ሐዘን ነው ውበትሽ ውበት ነው ፍቅርሽ
ብርሃን ጥለት አልቦ ከል ነጠላሽ
ዐይኔን የገለጠው ጥቁር ጨለማሽ፤…
        ሐዘንሽ አመመኝ
        ብሶትሽ ጠቀሰኝ ።

ደበበ ሰይፉ በዘመኑ ውስጥ የታዩ አድር ባዮችን በኃይለኛ ቃላቶቹ ውስጠ ህሊናቸውን ይቆነጥጥ ዘንድ ደግሞ ደጋግሞ የፃፈ ባለቅኔ ነው። በ1966 ዓ.ም. ከመጋቢት ወር እስከ ሰኔ በነበረ ጊዜ ውስጥ ወደ ስልጣን እርካብ ላይ ተንጠልጥሎ በህዝብ ትከሻ ላይ ለመፈናጠጥ ከጅሎ የነበረውን ምሁር አንደበቱ የሚንቀሳቀስ አፈ ጮማ ምሁር ለማጋለጥ ህሊናውን ለማቁሰልና ለመቆንጠጥ ሲል «ድንገት በቀል ፈላስፋማ አርበኞችን» ፃፈ።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

## የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

«…ታዲያ ዛሬ ፡ አስተናግር እንደበላ
ሺ ምላስህን ብታቁላላ እልፍ ትናጋህን ብታላላ
ሻካራው ልብ-አንደበትህ ፡ በአራራይ ዜማ ቢላላ
ለማኙን ቀርቶ ጥላውን ፡ ለማቀፍ እጅህ ቢያደላ
…ነቀዝ እንደበላው እህል ቀለህ
ዋግ እንደመታው መኸር ሻሽረህ
መልሕቋ እንደ ጠፋ መርከብ ሰፊህ
የትም ነፍሰህ…የትም ባክነህ…የትም ደቀህ»

የደበበ ብዕር እምቅ ኃይል ነበልባላዊ ቁጣ እንደነነድጓድ ያለ ድምፀት ያለው ሲሆን ከሀሊና ውስጥ ገብቶ መሰርሰር ብቻ ሳይሆን ድፍረት፡ እምነትና ተስፋ የተቀላቀለው በመሆኑ ከዘመን ዘመን የመሸጋገር ጥበባዊ እሴቱ ዛሬም ትናንትም ነገም አሌ የማይባል ነው።

ያየ የታዘበውን ልቡን ያደማውን ተስፋውን የበላውን የዘመኑን ድፍረት በቃላት ምጣኔና በልብ አገላለፅ ለመጨው ትውልድ ማስተላለፍ እራሳቸውን ከሚያውቁ ሰዎች የሚጠብቁ ድርጊት ነው። ብዕረኞች ተሸፋፍኖ መኖርን አይወዱም፡ የተሸፈነውን ገልጠው የተደረበውን እምቅ በፀሐይ ማንቃቃትን ያውቁበታል። ልክ ደበበ በ1965 ዓ.ም. እንዳደረገው 1965 ዓ.ም. ልክ እንደአሁኑ በምድረ ኢትዮጵያ አስከፊ እረሃብ ነበር የፊውዶ ስርዐት ባለስልጣናት ደግሞ ይህ እረሃብ እንዲሰማ አይፈልጉም ምክንያቱም የስልጣን መንበራቸው ይንቀጠቀጣልና ነው። በእርግጥ ያኔ እንዳሁኑ ስምንት ሚሊዮን በአስከፊ ሁኔታ በረሃብ አደጋ ውስጥ አልነበረም። ወደ 1 ሚሊዮን ሕዝብ ተርቧል የሕዝቡን መራብ የሚያውቁ ምሁራኖች ግን ሕዝቡ መራቡን እያወቁ መናገር በሌላ መልኩ ገዥውን ማስከፋት አድርገው ይቆጥሩት ነበርና እጃቸውን አጣጥፈው ተቀምጡ። ያኔ ደበበ ሰይፉ በምሁራኖቹ ላይ ቅሬታ እንዳለው ለማሳየት ብዕሩን አነሳ ፡ እርም በሌለው ወረቀት ላይ «አዬ! የኔ ዝምታ ጋግርት» ብሎ ፃፈ ፡ ከርዕሱ ስር እንዚህን ስንኞች አተተ።

«…ሆን ብዬ በጆሮዬ ላይ ተኝቼ
የልቤን ወያኔነት ቀጥቼ
ፍርሃትን-አብሮ አደጌን ተማጥኜ
እኔው የኔኑ ድምፅ ተሠቅቄ
እኔው የኔኑ ልሣን አፍኜ ፤
ሲጎነትሉኝ ጸጥ እርጭ
ሲነካኩኝ ጭጭ ምጭጭ።
አዬ የኔ ዝምታ ጋግርት
አይወልድ ቃል-አጥንት…»

ኢትዮጵያ አንድነቷ ተጠብቆ ድንበሯ ፀንቶ ታሪክ ከዘላለም እስከ ዘላለም ህያው ሆኖ ይኖር ዘንድ የጀግኖቿ አጥንት ከአስማና ተራ ጋር ሆኖላታል። እንዲህ «ጉማ ማንጉግ» ታሪክ አፍላሽ በዘር ተንታኝ በጎጥ ጉድ ላይመጣበት ከቶም



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

<u>የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም</u>

እንዳይመጣበት ወጣት ጀግኖቿን አሳልፋ ፈፋ ለፈፋ ጠላቶቿን ሲያሳደዱ በ1970 ዓ.ም. ደበበ እንዲህ ብሎ ፅፏል።

…በቀበሮ ጉድጓድ ላሉቱ
«…በቀበሮ ጉድጓድ ቀበሮ መስሏቸው
ውሾች አጓሩ በዛ ጩኸታቸው
አየሩን በከለው
ምድሩን አገረኘው-ትፋት ድንፋታቸው ፡
አይ የውሾች ነገር ፡
ማን በነገራቸው
ማን ባስተማራቸው
አንበሳ እንደሆነ የሚጠብቃቸው…»

ይህን ሰው ነው የዛሬ ሰባት ዓመት ሚያዝያ 16፣ 1992 ዓ.ም. ያጣነው። ኢትዮጵያ ምርጥ ምርጦቿን፤ አንጋፋ አንጋፋዎቿን ሰዎች በተከታታይ አታለች። ደበበ በሞት ቢለየንም ግን እኛ ጋር የሚቀር ህያው ስራው ከዘላለም እስከ ዘላለም አብሮን አለ። ደበበ ሰይፉ የብርሃን ፍቅር በተሰኙ የግጥም መድበሎቹ ውስጥ ምሁሩን ከሸነቆጣቸው ግጥሞቹ «ድንቄም መምህር» ግጥሙ እነሆ።

**ደንቄም መምህር**

ራሱን ሲከሽን
ሲያንቆለጳጵሰው
ማር-ወተት ሲያረገው
ከንፈሩን ሲስመው
ሊያስተምረኝ መጥቶ ፤
ብሽቅ አደረገኝ
የተረብ ጋዘና መሆኑ ሰቀቀኝ።
ለጋ ጊዜዬ ላይ መሸናቱ ነደደኝ።
እንዳይሰማው ፈርቶ
ልቤ አንሾካሾከ ፤
“አስተምረኝ ባለ
ስንት ነገር አለ !”



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

*የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም*

# ክፍል አራት

## ደበበ ሰይፉና ሥራዎቹ ሲታወሱ

በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ለበርካታ ዓመታት በመምህርነት ሲያገለግል የነበረውና ለተወሰኑ ዓመታት ታሞ ከቤት ውሎ የነበረው አቶ ደበበ ሰይፉ ሚያዝያ 16 ቀን 1992 ዓ.ም. ከዚህ ዓመት በሞት መለየቱ ሲሰማ ለሥነጽሑፍ ሰዎችና ለተማሪዎቹ ታላቅ መርዶ ነበር። ምክንያቱም ደበበ ሰይፉ በመምህርነቱ፡ በሐያሲነቱ፡ በጸሓፌ ተውኔትነቱ፡ በገጣሚነቱ፡ በሥነጽሑፍ ተመራማሪነቱና ተርጓሚነቱ ለሀገሩና ለወገኑ ያደረገው አስተዋጽዎ አመርቂ ከመሆን አልፎ በአፀደ ሥጋ የመቆየት ዕድሉን ቢያገኝ ኖሮ ለኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ ዕድገት የመጠቁና የላቁ ሥራዎችን ለማበርከት ይችል ስለነበር ነው።

ለሀገራችን ሥነጽሑፍ ዕድገት ጥልቅ ምኞትና የነበረው አቶ ደበበ ሰይፉ የተወለደው ሐምሌ 5 ቀን 1942 ዓ.ም. በሲዳሞ ክፍለ ሀገር በይርጋለም ከተማ ነው።

ሚያዝያ 17 ቀን 1992 ዓ.ም. የዛሬ ሰባት ዓመት በአዲስ አበባ ቅዱስ ዮሴፍ ቤተ ክርስተያን ዘመድ አዝማድ ወገኖቹና አድናቂዎቹ እንዲሁም ተማሪዎቹ በተገኙበት ተፈጽሟል። ደበበ ሰይፉ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን በይርጋዓለም ከተማ ራስ ደስታ ትምህርት ቤት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ በአዲስ አበባ ኮከበ ጽባሕ ትምህርት ቤት በ1959 ዓ.ም. አጠናቋል። በ1965 ዓ.ም. ደግሞ መጀመሪያ ድግሪውን በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ማዕረግ የተቀበለ ከመሆኑም ባሻገር በ1972 ዓ.ም. በእንግሊዘኛ ሥነጽሑፍ ሁለተኛ ድግሪውን (የማስተርስ ዲግሪውን) በማዕረግ አግኝቷል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

## የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

አቶ ደበበ ሰይፉ ከ1966 እስከ 1985 በኢትዮጵያ ቋንቋቅዎችና ሥነ ጽሑፍ በቴያትር ጥበባት ክፍል በመምህርነትና በሊቀመንበርነት ሠርቷል። በሥራ ታታሪነቱም የረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ አግኝቷል። ከ1986 እስከ 1989 የኢትዮጵያ ደራሲያን ሊቀመንበር በመሆን ለሀገሩ የላቀ ግልጋሎት አእበርክቷል። ከሥራዎቹ ውስጥ የቲያትር ጥበብ ከጸሐፌ ተውኔቱ አንፃር፣ ማርክሲዝምና የቋንቋ ችግሮች፣ ዕጌሬዳ ብዕር በሚል ከሌሎች ገጣሚያን ጋር የተዘጋጀ የግጥም ስብስብ፣ የብርሃን ፍቅር ቅጽ አንድ እና ሁለት የግጥም መድበሎቹ ሲጠቀሱ ሲቋጠር ሲተረተር፣ ዕድምተኞቹ፣ እሷና እነሱ፣ ከባህር የውጣ ዓሣ፣ እናትና ልጆቿ እና ሌሎች የተውኔት ሥራዎቹን ደርሶ ለመድረክ አብቅቷል።

የሀገራችንን ማኅበራዊ ሰሐ ለመንቀስና የዓይን ጉድፋችንን በብዕር ወረንጦ ቆንጥጦ ለማውጣት አስተውሎቱ ከነበራቸው ገጣሚያን ውስጥ አንዱ የሆነው ደበበ ሰይፉ በግጥሞቹ ውስጥ ያነሳቸው ቁም ነገሮች ለዕድገትና ለሥልጣኔ የሚበጁ የሀገር ፍቅርን ስሜት የሚቆሰቁሱ ናቸው። ገጣሚው ብርሃናዊ ራዕይውን ለተወለደበት ለይርጋዓለም ከተማ ጭምር ሲፈነጥቅ እናያለን። ደበበ ይርጋዓለም ከእንቅልፏ እንድትነቃና የዕድገት ትንሣኤ እንድታደርግ እንዲህ ይላል።

### ይርጋ ዓለም

ይርጋ ዓለም
ዋ..ይርጋ - ለም
የልጅነቴ ሕልም ቀለም
ዐይኔን የከፈትሽው ጨረር
ወርቃማይቱ ጀንበር።
ዕፀዋት፡ ሥራሥር፡ ፍራፍሬ
ዶቅማ፡ ጐደሬ፡ እንጆሬ፣...
የቅጠል እንግዳ የኩልቤት፡
እንሰት ቡና ፡ ቡና እንሰት
        ሲያልብሽ ሲያከናንብሽ
        ሲሞሽርሽ ሲያደምቅሽ
                ላያከብርሽ ፣
        ካባውን ሲያጠልቅልሽ
                ላይሾምሽ ፡
ዛሬ ባስተውል ታዘብኩሽ ።

የተፈጥሮ እምቢልታ ጥሩንባ
አረንጓዴ ቢጮህ ባንች አምባ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

## የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

ማንስ ነቀቶ ፡ እህ ሊልሽ ?
ማንስ በቅቶ ፡ ሊታደግሽ ?
ናፍቀሽኝ እንደ ገሠገሥኩ
አጠገብሽ በደረስኩ
ጭቃ. . . ኮረት
ፍራሽ. . . ዝገት
        ሁነሽ ሳገኝ
        ምን ይዋጠኝ ?

አባ ወራው እንደ ሞተበት
ወራሽ እንዳለማበት
        ገፊ ቤት ፡
ሲያይ ስትዘነጣጠይ
እሚጠግንሽ ጠፋ ወይ ?
ሰዎችሽ ሸሹን ፡ ሔዱን ?
ወደ ደራበት አመሩን ?
እንደ አሮጌ ጨርቅ ሲጥሉሽ
ማን ይጠቃቅምሽ አሉሽ ?
በቅሬታ ታዘብኩሽ ።

አንቺ ብቻ የማትቀልጪ
በላብ በወዝ የማትበልጪ ፡
        ለምን ?
ድጅኖ መዶሻ አካፋ
ጠረኑስ ካንቺ የጠፋ ፡
        ለምን ?
ባጥቢያሽ የገደል ማሚቶ መተኛቷ
በቦዘን ምክንያት መደፋቷ ፡
        ለምን ?. . . እኮ ለምን ?
ምፅዓትሽ አይቆጠር
አልሞትሽም እሚሉ ነገር ።
አለሽ እያሉ ሲቀብሩሽ
በቅሬታ ታዘብኩሽ።

ግዴለሽም ፡ ብሶትሽን አትደብቂ
ጉልበትሽን አበራቺ ፡ አነቃቂ
ፍቅርን በወዝሽ ሰንቂ ።
እንዳሸለብሽ እንዳትቀሪ
ነቃ ማለቱን ድፈሪ ።
ዕፅዋቱን ተመርኩዘሽ
ተነሽ. . . እባክሽ ተነሽ ፤. . .
ይርጋ ዓለም
ዋ.......ይርጋለም



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

የልጅነቴ ሕልም ቀለም
ዐይኔን የከፈትኸው ጨረር
ወርቃማይቱ ጀንበር።
1964

ኪነጥበባዊ ለዛ በተላበሰ ብዕሩ ከፈጥራቸውና በብዙዎች የሥነጽሑፍ አፍቃሪዎች ዘንድ ታዋቂነትንና ተወዳጅነትን ከአተረፉለት ሥራዎቹ ውስጥ ደግሞ በአዲስ የቃላት ግንባታ የተቀመመችውና በለዛና ሥላቅ የደመቀችው ልጅቱ የዘመነችቱ ትጠቀሳለች።

## ልጅቱ - የዘመነችቱ

ልጅቱ - የዘመነችቱ
ጧቱን ብድግ ንሥት
ትለውና
ፊቷን ትጥብ እሽት
ፍትግ ፍትግትግ
ዱሩላዋን ልቅቅ ጥፍት
ሌላ ምናምን ዱቅት
ሽፋሏን ቅልም ጥቁርት
ከንፈሯን ቅብት ቅልት
ታደርግና፤
ልጅቱ - የዘመነችቱ
ሱሪዋን ልምምቦቻሙን - ሱርት
ጫማዋን ነጠላውን - ጭምት
ቀበቶዋን ሰፊውን - ቅብትት
ጃኬቷን የቆዳውን - ጅክት



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

**<u>የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም</u>**

ታደርግና፤
ልጅቱ - የዘመነችቱ
መስቷቱ - ትልቁ መስቷት ፊት
ትቆምና፤
ሣቅ ግጥጥ...ሣቅ ግጥጥ...ሣቅ
ደርሶ ፍልቅ...ፍልቅልቅ...ፍልቅልቅልቅ
ከንፈር ገጠም...ደሞ ከፈት...
ደሞ ገጠም...ገጠምጠምጠም
ወደኃላ ሒድት...ሒድት
ደሞ ምልስ...ምልስ...ምልስልስልስ
ሽንጧን ሰበር...ቅልስ...ቅልስልስልስ
ዳሌዋንም ውዝ ውዝ
ቂብ ቂብ...ቂንን ቂንን
ክው ክው...ጅንን ጅንን
ደሞ ፈገግ...ደሞ ቅጭም...ቅጭምጭምጭም
ዐይኗን ከፈት...ደሞ ጨፈን...ስልምልምልም
ደሞ ጉርጥ...ደሞ ጥቅስ...ደሞ ጉልጉል
(በራሷ ትቀልድ ይመስል)
ልጅቱ - የዘመነችቱ
ፕሮቫው ብሎ ጥቅልል
ወደ ቁርሷ መለስ ስትል
እማማዋ ንድድ ቁጥት
ትንሽ እህቷን ጥርት
በኩርኩም ግጭት!
"ገና ካሁኑ ይወጣብሽ
ለምነው ጧት መነሣትሽ?"
ደሞ ማለት።
አባባዋም እዝን ቁጭት
ጸሎታቸውን ዝንግት
"ወይ ጉድ መበላሸት"
አርዝመው እያዩ ማለት።
ልጅቱ - የዘመነችቱ
ገራብ ገራብ እያለች
እማየዋን እያሣቀለች
አባዬዋን እየገረመመች
ቦርሳዋን እንደ ቦረሰች
ላስቲክ ብጤ ነገር ባፍዋ እያላመጠች
እያንቀጫቀጨች
ርፍድ ብሎባት ችኩል ችኩል እያለች
እሁድ ጧቱን ባንድ ሰዓት ውልቅ ያለች
(አፍታም ሳትቆይ - ወድያውኑ)
ሰኞ ጣቱን ምልስ ትላታለች።
ልጅቱ - የዘመነችቱ።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

1966ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የቋንቋዎች ተቋም ከደበበ ሰይፉ ጋር ሥነ ጽሑፍ ሲያስተምር የነበረውና በ1992 ዓ.ም. በታተመው በብርሃን ፍቅር ቅጽ ሁለት የደበበ ሰይፉ ግጥም ላይ መግቢያ የጻፈው አቶ መስፍን ሀብተማርያም በአንድ ጋዜጣ ላይ ስለ ደበበ ተጠይቆ በሰጠው አስተያየት "...ጥሩ ገጣሚ ባለቅኔና መምህር ነበር ። ከሌሎች ለየት ያለ ብዙ የእንግሊዘኛ ግጥሞች ስለነብሩት በየጊዜው ያነብልኝ ነበር ። በእኔ አስተያየት ደበበ ለኖቤል ፕራይዝ ይወዳደራል ብዬ የማስበው ምሁር ነው። ደርዝና ጥልቀት ያላቸው የእንግሊዘኛ ግጥሞቹ ይማርካሉ።

" ደበበ ገና የአሥራአንደኛና የአሥራሁለተኛ ክፍል ተማሪ ሳለ የቀድሞው ብስራተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያ የአጭር ልብ ወለድ ውድድር አዘጋጅ በነበረበት ወቅት ተወዳድሮ አንደኛ ወጥቷል ። ሽልማትም አስገኝቶለታል ። በአሥራሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ያለፈው በማዕረግ ነው። ከዚያም ለከፍተኛ ትምህርት ቢዝነስ ኮሌጅ ገባ። ነገር ግን እስከ አንደኛ ሴሚስትር ድረስ ከተማረ በኋላ የትምህርት ጊዜውን አቃጥሎ በሚቀጥለው ዓመት ወደ ኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ተቋም ገባ። ይህ በሀገራችን የተለመደ ሳይሆን የጥበብ አፍቃሪነቱን ያሳያል። ምክንያቱም የእርሱ የህይወት አቅጣጫ የተቃኘው በኪነ ጥበብ ዙሪያ በመሆኑ ነው።

"ረጅም ልቦለድ ለመጻፍም ይመኝ ነበር። ሞት ባይቀድመው እንደሚሳካለት አልጠራጠርም። ደበበ መምህርና ባለቅኔ ብቻም አልነበረም። ሁለገብ ምሁር እንጂ። በልቦለድ በቲያትር በግጥምና በብዙ የጥናት ምርምር ሥራዎች ለወገኑ ታላቅ ቁም ነገር ያበረከተ ሰው ነበር።

"በሰብዓዊነቱ አኳያ ሲታይ እጅግ ሩኅሩኅ ጥሩ መካሪ ለሰዎች ቀና ምኞትና ፍቅር ነበረው።" ብሏል።

የደበበን ሰባዓዊነትና ርኅራኄ ከሚያሳዩት ግጥሞች «በቢኤ ዲግሪ በተመረቀች በሶስተኛ ወሯ ለሞተች ዐይነሥውር ተማሪዬ» በማለት በ1977 ከጻፈውና በብርሃን ፍቅር ቅጽ ሁለት «ኒሻን» /የልጅቱ ስም ይሆን?/ የሚለው ግጥሙ እነሆ፡

## ኒሻን

ኒሻን
ዕጹብ ብርሀን
ትሁት ታጋይ፣
ጨለማን ያህል ፈያታይ
ቢጠለልም ካንቺው አምባ፣ አደባባይ
ካንቺው ሥጋ፣ ካንቺው ዐዋይ፣
ሰለባ አልጣለሽም ነበር፣ ግዳይ
ሽንፈት አልገባሽም ነበር፣ ስቃይ
ጩኸት አልወጣሽም ነበር፣ ብካይ።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

## የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

ያይነሥጋን ሕፀፅ ድክመት
የጨለማን ግርዶሽ ጥለት
ገፈሽ፤ በልቦና ብርሃን ውበት
ጥለሽ፤ በመንፈስ ፀዳል ፍመት
አልፈሽ፤ የቁም ሞትን ያህል ኬላ
ዘለሽ፤ የተስፋ - አልባን አጥር - ባላ፤
ተተግነሽ ከዕውቀት ምስካይ
ይህን ሕይወት ሚሰኝ ቀላይ
የስንት ኅበዝ ትርክዛ አስጣይ
ተግተሽ ስትዘፍቂው ስናይ፤
ያን ሁሉ ጥናት፤ ያን ሁሉ ብቃት
ያን ሁሉ ብርታት፤ ያን ሁሉ ምላት
እንዴት ብለን፤ መች ጠርጥረን
ሞት በድንገት ይነጥቅሻል ብለን?
ኒሻን
ዕጹብ ብርሃን
ትሁት ታጋይ፤
ጨለማን ያህል ፈያታይ
ቢጠለልም ካንቺው መደብ አደባባይ
ካንቺው ሥጋ፤ ካንቺው ዐዋይ፤
ሰለባ አልጣለሽም ነበር፤ ግዳይ
ሽንፈት አልገባሽም ነበር፤ ስቃይ
ጩኸት አልወጣሽም ነበር፤ ብካይ።

ደበበ ፍቅር ከቂም፤ ከጥላቻ፤ ከከንቱ ውዳሴ በላይ ዐቅም አለው ብሎ ያምን እንደነበር ይቅርታ በሚለው ግጥም በኩል ይናገራል።

«ጎሊናዬ ያንጎራጉር ዐይኔ እንባ ያውርድ፤
በድያለሁና ጓደኛና ዘመድ።
እንደዕኑ ቋጥኝ ጎርፍ እንዳይገፋው
ግጭትን ለመናቅ ፍቅር ዐቅም አለው።

አቤት ባይ ሲመጣ
ይቅር ላለማልት ጆሮህን እንዳትሰጥ፤
በርህን ስትዘጋ ጥሪው ውጪ ሲቀልጥ፤
አቤት ባይ ስትሆን ድምጥህ እንዳይቋረጥ።»

ደበበ በግጥሞቹ ሁልጊዜ ሌሎችን ነው የሚመለከተው። ራሱን ፃድቅ እያደረገ ማቅረቡን አይችልበትም። ስለራሱም ከጠቀሰ በሚከተለው መንገድ ነው።

### ራሴን በላሁት



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

ገብቼ ሱባዔ
ከብቻ ጉባዔ
ላያሌ ዓመታት
በእኔነት ማሳ ተመላልሼበት
ወጥቼ ወርጄበት
አዝመራ ባጣበት
ራሴን በላሁት
እየመነዘርሁት
እያመናዘርሁት።

ወደፊት የተለያዩ ምሁራን ስለ ደበበ ሰይፉ የሕይወት ታሪክና ሥራዎቹ የተሻለ ጥናታዊ ጽሑፎችን እንድሚያስነብቡን ተስፋ አለን።

## ዘመዴን ስስመው

ዘመዴን ስስመው ፤
ጉንጩ ቢሻክረው
እኔንም ሻከረኝ ፤
ዕድሜ መለስለሱ ማብቃቱ ታወቀኝ።

ከበደ ገብረሃና እንዳሉት እኔም ባሰብኳት ቁጥር የእንባ ከረጢቴን የምትሸነቁርብኝና በፀፀት የምታንገበግበኝ ግጥሙ ይቻትላችሁ።

## ለምን ሞተ ቢሉ

ለምን ሞተ ቢሉ
ንገሩ ለሁሉ
ሳትደብቁ ከቶ ፤
"ከዘመን ተኳርፎ
ከዘመን ተጣልቶ።"

1968

ደበበ ብዙ የሚነገርለት ሰው ነው! ብዙ ግፍ ተውሎበታል! 20 ዓመት ባገለገለበት ስታፍ ውስጥ ምንጣፍና ወንበሩን የሚያስረክብለት ወዳጅ አጥቶ የጡረታ አበሉን ሳያገኝ ያለፈ ሰው ነው። ስምንት ዓመት ሙሉ ታሞ ሲማቅቅ በመጠየቅና በመርዳት ፊንታ «አብዱል» እያሉ ሲያውሩበት የነበሩ የቅርብ ጓደኞቹ ነበሩ። ወጣቶች ግን የደበበን ሀውልት በልባቸውም ባደባባዩም ያቆሙለታል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

*የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም*

## ክፍል አምስት

### የክፍለ ዘመኑ ገጣሚ፤ የክፍለ ዘመኑን ግጥም ትቶልን አለፈ

ደበበ ሰይፉ ግጥሞቹ ትንቢታዊንታቸው ሁሌም ቢነበቡ፡ ቢተረኩ ወቅታዊነታቸውን አመልካች ናቸው። አሁንም። በ1966ዓ.ም. ጽፎት በ1992ዓ.ም. ለህትመት የበቃውና ያስነበበን «ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ» ዛሬም እውነታው እውን ነው። ይህን ግጥም አዋቂዎች በምትዓመት አንዴ የሚገኝ ግጥም ይሉታል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ ከ33 ዓመት በኃላ ዛሬም ሲነበብና ሲተረክ እውነታው አለ። በጥቅሉ ለራስ ሳይሆን ለሀገር፤ ለህዝብ የተጻፈ ደብዳቤ ማለቱ ይቀላል።

ደበበ በግጥሙ እንደዘመረው፤ ዛሬም ለዚህ አምባ ለዚህ ዘመን ይታዘናል።

ሰው ከልማዱ ተቀነሰ፤ ከባህሉ ተራቆተ
መኖር ምን እንደሆነ ሳተ፤
በገዛ ታሪኩ ተረተ።

ዛሬም ያለ ክስተት ነው።

ደበበ ግጥሞቹ ሕዝባዊ ናቸው። ለቅሶው ስለ ወገን ነው። የብዕሩ አርማ፤ የህሳቡ ባንዲራ ሰው
ነው። ናፍቆቱም።

ይኖር ይሆን አርማ፤ ይኖር ይሆን ወይ ባንዲራ፤
ሰውን የመሰለ ቀለም ያለው ሰውን የመሰለ አሻራ፤
እማይወድቅ፤ እማይታጠፍ ሰንደቅ
እማይከስም፤ እማይዳፈን ደመራ?...
የሚል ይሆናል።

ዐይን ያለው ይይ!
ልብ አለው ያስተውል!
ጆሮ ያለው ይስማ!

እንዳለው በግጥሙ እስቲ ልብ ብላችሁ ትከታተሉ ዘንድ «ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ» እነሆ፡
ግጥሙን አክባሪውና አድናቂው ተማሪው ግርማ ደገፋ በአንድ ውቅት በአንድ ዝግጅት አቅርቦት ለዚህም ክፍል ይቀርብ ዘንድ ለአደረገው ትብብር ምስጋና ይድርሰውና «ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ» ግርማ ደገፋ እንዳነበበው።

**ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ**

## ደበበ ሰይፉ ለኪነጥበብ ተወልዶ ለኪነጥበብ የሞተ

እንደ ተማሪውቹ አጠራር ጋሼ ደበበ እንዲህ ይላል ስለ ግጥሞቹ፡



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

“የዕድሜዬን ግማሽ ለሚያህል ጊዜ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ በተማሪነትና በመምህርነት እንደመቆየቴ፣ የምሁራንን ጉዳይ የግጥሞቹ ጉዳይ ያደረኩበት ጊዜ ጥቂት አይደለም። ለምሳሌም ከቅድመ-አብዮት ግጥሞቹ መኻል፣ “ድንቄም መምህር”፣ “ጥሬ ጨው”፣ ”ሰማይና ምድር”፣ “እማማ...እማማዬ” እና “ያባትህ ልጅ” የተሰኙት በቀጥታ ምሁር ነክ ጉዳዮችን እሚያወሱ ሆነው ነው እምታገኟቸው። በተለይም የመጨረሻዎቹ ሁለት ግጥሞች የወቅቱን የተማረ ትውልድ ሀገርተኛነትና ሕዝባዊነት እሚጠይቁ ናቸው። በፊውዶ ቡርዣ መስፈራሮች ሥርዓት መወግሸቱንና የማንነት መለዮውን መጣሉን እሚያንጐራጉሩ። ይህ ይሁን አንድነታቸው እንጂ ጉልህ ልዩነትም በመኻላቸው አለ። “እማማ...እማማዬ” ሀገረኛ መለዮውን አጥቶ የነበር ትውልድ የፀፀት እንጉርጉሮ ነው። በሌላ ገጹም የራስ ግንዛቤ የተሐድሶ መዝሙር። “ያባትህ ልጅ” ግን፣ “አንቺ ልጅ ኩሪባቸው በእንግሊዘኛ አናግሪያቸው” የተሰኙትን ስንኞች የዘፈነውን (ያዘፈነውን) ትውልድ ረግራጋማነትን ባንድ ፊት፣ በሰማየ ሰማያት “ቋንቋ” ካልሆነ በባላገር ልሣን አንደበታችን አይጨቀይም (ምድራዊ አይሆንም) ይሉ የነበሩትን አንዳንድ የቀድሞ ሊቃውንት መሠሪነትን በሌላ ፊት፣-ብሃንጸር የተወረወረ የታዛቢ ቁጣ ነው፣ በትር። በተረፈ በሁለቱም የሀገርተኝነትና የሕዝባዊነት ድምፆች ቢሰሙም፣ በመጀመርያው ሀገርተኝነት ነው ይበልጥ እሚጐላው። በሁለተኛው ደግሞ ሕዝባዊነት።

“ይኸው ጉዳይ በድኅረ አብዮት ግጥሞቹም ውስጥ መዛመቱና መከሠቱ አልቀረም። ምሳሌ ቢያስፈልግ “ሐዘንሽ አመመኝ” ንና “ለድንገት - በቀል ፈላስፋማ ዐርበኞች” የተሰኙትን መጥቀስ ይቻላል።

“ሐዘንሽ አመመኝ” እንደ “እማማ...እማማዬ” ሁሉ ከተማረው ትውልድ መኻል በሥጋም በመንፈሥም ከሀገሩ ርቆ የነበር ወገን እሚያሰማው የቅሬታ እንጉርጎሮ ነው። የብክነት ዐይነጥላው ተገፎለት ራሱንና ሀገሩን ማተኮር ሲጀምር ከውስጡ እሚብሰከሰክ የነፍሱ ጩኸት ነው፦ የናፍቆት፣ የፀፀት እሮሮው፣ በሌላ በኩል ግን፣ በሱና በየሱነቱ (ማለት በሀገሩ) መኻል የቆመውን ማንኛውንም ገደል አፈራርሶ፣ እሱነቱን (የሱነት መለዮውን) የመፈለግና የማግኘት ቁርጠኝነቱ እሚሰማበት የብሩህ ተስፋው መዝሙር ነው።

እርግጥ ነው “ሐዘንሽ አመመኝ”፣ እጅግ አያሌ ኢትዮጵያውያን በረሀብ በሚረግፉበት ወቅት እንደ መሆኑ፣ ከሌላኛው ግጥም ይበልጥ ስሜትን ሊጫን ይችላል፣ ሊያም። ሆኖም ብሥራት ፍጹም የተለየው አይደለም፣ ውጋጋን። ቀቢፀ - ተስፋ ያደቀቀው ትውልድ ድምፅም አይደለም፣ ከቶም።

ሁለቱም ግጥሞች የተማረው ትውልድ ዐይን ላይ ወድቆ የነበረውን መንታ ጭምብል ያሳያሉ። ማሳየት ብቻ ሳይሆን ጭምብሉ በተራው ሲወድቅ፣ ትውልዱ ወደ እውነታው እውነት ለመቅረብ መብቃቱንም ያበሥራሉ። በ”እማማ ...እማማዬ” ሀገሩን ባዶ ማጀት አድርጐ ይገምት የነበረው ትውልድ፣ ቆይቶ መልካም ገጽታዋን ያያል። በ”ሐዘንሽ አመመኝ” ሀገሩ ሁሉ በጅዋ ሁሉ በደጅዋ ትመስለው የነበረው ትውልድ፣ የሚያስበውን ያህል እንደሌላት ያስተውላል። ዋናው ቁም ነገር፣ ሁለቱም ከጽንፋዊ አተያዮች ተነሥተው እሚደርሱበት ግብ አንድ መሆኑ ነው። ከራስ ጋር -



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

## የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

ከሀገር ጋር ዕርቅ። ይህም የግጥሞቹ እንጉርጉሮነት ሳይሆን መዝሙርነት ይበልጥ ጎልቶ እንዲሰማ አድርጓል።
በሌላ ረገድ፣ "ያባትህ ልጅ" እና "ድንገት - በቀል ፊላስፋማ ዐርበኞች" እሚመሳሰሉበት ነጥብ አለ፣ እሚናጸሩበትም። ሁለቱም ከተማረው ዘመናዊ ትውልድ መኻል አንዳንዱን እሚያስታዝቡ ናቸው፣ ሕዝባዊነቱን እሚጠይቁ። ይህም ሁኖ "ያባትህ ልጅ" ዕውቀቱን በአንደበተ - አፍርንጅ ከብዙኃን እንዳይደርስ ያደረገውን ምሁር በስላቅ የሚሸነቁጥ ሲሆን፣ ድንገት በቀል ፊላስፋማ ዐርበኞች" ደግሞ፣ በተለይ ከ1966 መጋቢት እስከ ሰኔ በነበረው ጊዜ ከሥልጣን ርካብ ተንጣጥሎ ከብዙኃኑ ሕዝብ ላይ ሊፈናጠጥ ከጅሎ የነበረውን አንደበተ ነቀልቃል ምሁር ይሞግት ሲባል የተጻፈ ነው፣ ያጋልጥ። ህሊናውን ይውቀስ ሲባል የተወረወረ ነው፣ ይቆንጥጥ።"

ደበበ ጅምር ስራዎቹን በጅምር ትቶ ዳግም ላይመለስ መሰናበቱ የብዙ ወዳጆቹንና የሙያ አፍቃሪዎቹን ሀዘን ይበልጥ እንዳከበደው መገመት ይቻላል።

ደበበ ገና የዩንቨርስቲ ትምህርቱን ጨርሶ ስራ እንደያዘ የጀመረውና ዛሬ ድረስ ተወዝፎ በጅምር የቀረ አንድ ታላቅ ሥራ አለው። ይህ ትልቅ ሥራ የአገራችንን ገጣሚያን ታሪክ ከነግጥሞቻቸው ጨመሮ የያዘ የግጥም አንቶሎጂ (በቅደም ተከተል ከጥንት እስከ ዛሬ) ጅምር ሲሆን በአብዛኛው የተጠናቀቀ ነው። ይህን የደበበን የግጥም አንቶሎጂ ስራ አሁን ባለበት ደረጃ ቢታተም እንኳ ትልቅ ዋጋ ያለው ሥራ እንደሆን የሚናገሩ አሉ። ታዲያ ይህን ሃላፊነት ወስዶ ማሳተም ቢቻል ለደበበ ስም ብቻ ሳይሆን ለአንባቢያንም ትልቅ ዳረጎት ነበር።

ደበበ በርካታ ባለ ብዙ ገቢር ተውኔቶች፣ አጫጭር ተውኔቶች እስከዛሬ ለመድረክ እድሉን ያላገኙ እንዳሉት ይታወቃል። በተጭማሪም ተጠናቀው ለአንባቢ ያልደርሱ በርካታ የትርጉም ሥራዎችና የእንግሊዘኛ ግጥሞችም የሚጥቀሱ ሥራዎቹ ናቸው።

ለእትመት ዕድሉ ያልገጠማቸው የደበበ ግጥሞች «የወእኒ ቤት አልጀብራ»፣ «የወፎች ጫጫታ» እና ሌሎችም በርካታ የግጥም መድበሎቹ ለእትመት በቅተው ለአንባቢ የሚቀርቡበትን እየናፈቅን፣ ጅምር ሥራዎቹ ተቋጭተው ለወግ ይበቁ ዘንድ የወዳጅ ዘመዶቹን፣ ይበልጡንም የሙያ ባልደረቦቹንና የቀደምት ተማሪዎቹን ጥረትና ተቆርቋሪነት ብሎም ቁርጠኝነት የሚጠይቅ ይሆናል። ብዕረኛው ደበበ ሰይፉ በሕይወት አለፈ እንጂ አልሞተም። ስሙና ሥራው ከመቃብር በላይ ህያው ሆኖ ከትውልድ ትውልድ ሲሸጋገር ይኖራል።

ደበበ ከእናቱ፣ ከወንድሞቹና ከእህቶቹ ጋር አብሮ ነበር የሚኖረው። ትዳር አልመሰረተም። ልጅም አላፈራም። ሥነ ጽሑፍ ነበር ትዳሩ። ኪነጥበብ ነበር ልጁ። እናም ለኪነጥበብ ተፈጥሮ ለኪነጥበብ የሞተ ታላቅ ሰው ነበር ደበበ ሰይፉ።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

## እማማ...እማማዬ

እማማ እማማዬ...
የኔነት መደብ መብቀያዬ
የኔነት መደብ አሻራዬ፤
እስቲ ፡ እንምከር እንወያይ
ገበናሽ ገበናዬ
ተፈልቅቆ እየታዬ።

ከማሕፀንሽ አምባ በቅዬ
መልክ ስምሽን ከመልክ ከስሜ አንጠልጥዬ
ግርማ ሞገስሽን ተካፍዬ
        ያለውለታዬ፤
ስሐሽን ተቀብዬ
        ያለዕዳዬ፤
ዕድልሽ ከዕድሌ ተቆራኝቶ
ገነቴ በገነትሽ ተመስርቶ
ፍዳዬም ከፍዳሽ ተጋርቶ፤
ምነው ታድያን ቆይቶ ይታየኝ ጀመር ተለያይቶ
ያዋደደን ገመድ ተፈቶ
ውጥሩ ረግቦና ላልቶ?
ምንድን ሆነ እማምዬ ፡ በማኻላችን ምን ነፈሰ
ቃልሽን ከቃሌ ያበሰ ፡ ውላችንን ያፋለሰ
ገጽሽን ከዐይኔ የገሠሠ
ምንድን ሆነ እማዬ ሆይ ፡ በማኻላችን ምን ነፈሰ?

ብትጠሪኝ እንዳልመልስሽ
ብትልኪኝ እንዳልላክሽ
ፈቴን አዙሬ እንዳልፍሽ
ብትቀርቢኝ እንድርቅሽ
ብታወሪ እንዳላዳምጥሽ
ብትጽፊ እንዳላነብሽ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

<u>የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም</u>

ውሸት ብዬ እንድሥቅብሽ
ተረት ብዬ እንዳገጥብሽ
ያደረግ ፡ ምንድን መዓት ተተኮሰ
ምንድን ሆነ እማምዬ ፡ በመኻላችን ምን ነፈሰ?
ቃልሽን ከቃሌ ያበሰ ፡ ውላችንን ያፋለሰ
ገጽሽን ከዐይኔ የገሠሠ
ምንድን ሆነ እማዬ ሆይ ፡ በመኻላችን ምን ነፈሰ?

እባክሽ ፡ ዘራችን በውል ይታወቅ
በወግ ይቆጠር አይደበቅ
በመጤ ተረብ አይታመቅ
በባዕዳን ክርን አይድቀቅ፤
እኔና አንቺን እሚያውቀን
የታሪክ ልሣን ይፍረደን ፡
ሲይዙኝ በጠይምነቴ
ፀሐይዋ አትሁን ምክንያቴ።

እማማዬ ፡
ከዱቃው ጋር ከአፈሩ
ከዳዴው ጋር ከእሹሩሩ
ከሕመሙ ከጭንቀቱ
ከቡረቃው ከሐሴቱ
ከበጋው ጋር ከክረምቱ
ከብርዱ ጋር ከሙቀቱ
የነበርሽ - የተካፈልሽ ፡
አሁን ወዴት ይሆን ያለሽ?
        በይ ፡ አምባሻ የለሽም ወይ ዳቦ
ጨጨብሳ የለሽም ወይ ጭኮ
ጐመን ፡ የለሽም ወይ ገንፎ፤
ያንቺን ገበታ ደፍቼ
ጽዋሽን በእጆቼ አንክቼ
        የባዕድ ማዕድ ስመጥን
        ወጥሽ ሻግቶ ይደፋን? ይደፋን?
                ጠላሽ ሾምጥሮ ይፍሰስን? ይፍሰስን?
ብፈራ ነው በሰው ምላስ
ቃናሽ ኋላ እንዳይዳስ ፤
ተራርቀን እንዳንቀረው
ተመዝነን እንዳናንሰው
ብፈራ ነው እማምዬ ብጨነቅ ነው።
የሕይወትሽ ማኅደር ብራና
እንደያዘ ያንቺን ዜና
ሳይገለጥ ቀን ያልፍና
ሳይነበብ ሳይወራ ይቀርና፤



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ
ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

እንዳይደድቡ ዐይኖቼ
ልብ ሕሊና ጆሮቼ
የሕያው ገጽ'ሽ ውበቱ
እንዳይነጣ ደም ግባቱ
ዐመዱ እንዳይቀር ሐውልቱ።
ብፈራ ነው እማምዬ ፡ ብጨነቅ ነው
ተራርቀን እንዳንቀረው
ተመዝነን እንዳናንሰው።

ካንቺ ርቄ - ከእኔ ርቄ
ከየምናምኑ ወድቄ
በሌላው ዕድር ጠልቄ
ልናገር ብል - ማን ሊሰማኝ?
ልጐብዝ ብል - ማን ሊያኮራኝ
እባክሽን፡ አስተምሪኝ አልተማርኩም
ጥላቻሽን ሳለመልም ፡ ፍቅርሽን ገና አላወኩም።
በአርያሽ መፈጠሬን
በለለግሽ መወሰኔን
መወለዴን ባንቺ ልደት
መቦረቄን ባንች ልጅነት
መፈንደቄን ባንች ተረት፤
- እንደምሞትም ያንቺን ሞት -
አስተምሪኝ አልተማርኩም
ጥላቻሽን ሳለመልም ፡ ፍቅርሽን ገና አላወኩም።

እማማ እማማዬ ፡
የኔነት መደብ መብቀያዬ
የኔው ቀለም አሻራዬ ፡
ነብሴን ልጣል፤ ካንቺው ጉያ - ካንቺው ገላ
ዳግም ከቶም አልሁንብሽ ተቀጥላ
የወግ ልጅ የይስሙላ።...
ቃል ኪዳኔን ትቀበይኝ
የኔ ሁኚ ፡ ያንቺ አድርጊኝ
አልለይሽ ፡ አትለኝ -
አይበድሉም ብበድልሽ
መቼም የትም እናቴ ነሽ... እናቴ ነሽ።

1964ዓ.ም.



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

*የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም*

## ሐዘንሽ አመመኝ

ውል አልነበረንም የፍቅር ቀጠሮ
ቃልም አላኖርንም በወግ ተቀምሮ፤
እኔ አንቺን እንዳላይ
አንቺ እኔን እንዳታይ አምባችን ተቃጽሮ
ዕጣችን ተካሮ፤
ቀለምሽ ከዐይኔ አሻራሽ ከጣቴ ባይጠፋ ተማትሮ
(እትብት እምብርት ሁኖ እንዲኖር ደድሮ)
ይኸው አካሄደን በድንገት ዘንድሮ።

የገጽሽ ብርሃን ቢጠይም ፀዳሉ
ድምፅሽ ቢቀጥንብኝ ቢሠልብኝ ቃሉ
ወዘናሽ ቢማስን ዛሬ ያለውሉ
በእጆችሽ ጨበጠኝ ሐዘንሽ ሥዕሉ

ሐዘንሽ አመመኝ
ብሶትሽ ጠቀሰኝ።

ጀንበር ነሽ አበባ ሕይወት ተስፋ ዘቦ
ፋሲካ ዕንቁጣጣሽ ማኅሌተ ገንቦ
በዩ ያወደስኩበት ታዘበኝ ዘመኔ የትላንታት ቀኔ
ዛሬ ሊጮህብኝ ቅኔ እንዳይደል እውኔ፤

ሐዘንሽ አመመኝ
ብሶትሽ ጠቀሰኝ።

የገደል ማሚቶን ታዘብኳት ተኝታ
በጩኸትሽ ማየል አኩርፋና ታክታ
ላንቃዋ ይታየኛል ደም ለብሶ ደም ጐርሶ
ቃልሽ ያለፈበት በጭንቅ ተለውሶ፤

ሐዘንሽ አመመኝ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

<u>የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም</u>

ብሶትሽ ጠቀሰኝ።

ጽጌሬዳይቱ ንቦችሽ አለቁ ሰዎችሽ ደቀቁ
ጨፌ ላይ ተኝተው ባድማ ላይ ነቁ፤
ዐዋይን ሰማኋት ስታለቅስ በይፉ
ከጐጆሽ ስትወጣ ትቢያዋን አራግፉ፤

ሐዘንሽ አመመኝ
ብሶትሽ ጠቀሰኝ።

አላውቅልሽ ብዬ አታውቂልኝ ብዬ
እምነትሽን ጥዬ ፍቅርሽን ገድዬ
አኩርፌሽ ስቀመጥ ያው እንደ ባላንጣ
ይኸው ነጭ ማተብሽ ሊያስታርቀን መጣ፤
ሐዘን ነው ውበትሽ ውበት ነው ፍቅርሽ
ብርሃን - ጥለት አልቦ ከል ነጠላሽ
ዐይኔን የገለጠው ጥቁር ጨለማሽ፤...

ሐዘንሽ አመመኝ
ብሶትሽ ጠቀሰኝ።

ግንቦት 1966ዓ.ም.



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

## ከአክሱም ጫፍ አቁማዳ

ትግራይ ላከ ወሎጋ አበድሮኝ ብሎ አንድ ቁና ጤፍ
ወሎም አፈረና የለኝም ማለቱን ባህሉን መዝለፍ
ቆሌውን መንቀፍ
ላከ ወደሸዋ ምናልባት ቢሰጠው ለሰው እሚተርፍ።
ሸዋም አፈረና የለኝም ማለቱን ወደሐረር ዞረ
ሐረርም መልሶ ባሌን አተኮረ
ባሌም ወደአርሲ፣ አርሲ ሲዳሞን
ሲዳሞም ተክዞ፣ ግን የለኝም ብልስ ማን ያምነኛል ብሎ
ወደጋሞ ላከ አቁማዳ ጠቅሎ።

ጋሞን ብርድ መታው ሐዘን ገባውና
የራሱን ምንዳቤ የግል ስቅየቱን ችሎት በጥሞና
በጋቢ ደቡኖ የልቡን ጠባሳ ሲኖር እንደደህና
ዛሬ የወንድሙን የእርዳኝ አቤቱታ መስማት አልቻለና።
አውጥቶና አውርዶ ላከ ወደ ከፋ እጅግ አስተዛዝኖ
ከሀፍረት ያድነኛል፣ ከረሃብ ያወጣኛል ሲል ባያሌው አምኖ።
ከፋ እንደደረሰው በድንገት አቁማዳው በነብሱ ዋይታ
ሐራራው ተሰማው የሥጋው ድንፋታ
በብልሀት አዛጋ ቆይቶ ቆይቶ የተስፋ ጥል ቀዳ
ሲልክ ከኢሉባቦር አበድረኝ ብሎ እህል በአቁማዳ።
ጭምቱ ይሉባቡር ይኖር የነበረ የቤቱን ጉድ ጓዳ
በሞኛሞኝ ገላው ቆዳው ውስጥ ወሽቆ
ጠየቀ ወለጋን ሐፍረቱን ደብቆ ኩራቱን ዘቅዝቆ።
ኬት አመጣ ብሎ ወደኔ ላከብኝ እያለ ወለጋ
እጅጉን ተደሞ
ሂደ ወደጎጃም ዛሬን ሁነኝ ብሎ ለማፀነው ቁሞ።
ጎጃምም ተሰምቶት፣ ሰቀቀን ሐዘኑ፣
ደረት እየመታ፣ ቅኔ እያወረደ፣ እንባ እያፈሰሰ
ወግና ኩራቱን በየቦዳው መሀል እየነሰነሰ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

ዐባይን ተሻግሮ ከጎንደር ደረሰ።
ፋሲል ላይ ተነጥሮ፤ ጎንደርም ሐዘን ላይ ነበረ ተቀምጦ
ተድላ ልጁ ሙቶ፤ ገናን ክንዱ ታጥፎ፤ በዘመን ትድጠ
ጎጃም መጣ ሲሉት የእዝን የተመኘን ልቡን በታዘበ
የኩራት ካባውን ሊጥል ባንጓበበ
የወንድሙ መምጣት፤ እቅጩ መንስዔ፤ መሆኑን ሲረዳ ረሀብ አበሳ
ጥንትም አልሆነኝም ከእንግዲህ ይበቃኛል ለይሉኝታ አልሳሳ
ብሎ ከኤርትራ እህል ለመበደር በርትቶ ተነሳ።

የዘመዱ እጦት ነበርና እጦቱ በዝቶ ሰቀቀኑ
ኤርትራ ታመመ ደም ጎረፈ ከዓይኑ
ወደትግራይ ላከ መላ ባገኝ ብሎ ከአደራ ደብዳቤ
"እባክህ ላክልኝ አንድ አቁማዳ እህል ልሞት ነው ተርቤ።"
ትግራይ አስተውሎ አቁማዳው የራሱ መሆኑን ለይቶ
ረሀብ ዕጣቸው የሁል ወንድሞቹ መሆኑን አካቶ
ሐዘኑ አነቀው፤ ትንፋሹ መረረው ትካዜ ሆዱ ገብቶ።
"እኔና ወንድሞቼ" አለ በለዘብታ
ለራሱ እንዲያወራ የራሱን ስሞታ፤
"እኔና ወንድሞቼ ሁላችን...ሁላችን
ከባዶ አቁማዳ ነው እሚዛቅ ፍቅራችን
ይህ ነው አንድነታችን
ይህ ነው ባህላችን
ዘመን ማዛጋቱ በያንደበታችን።
ለኋላ ትውልዶች ተረት እንዳይመስል ይህ ብካይ እሮሮ
ይህ ጠፍ ስብእና ይህ ስቁይ አእምሮ
እንዳኖረው ያሻኛል ይህንን አቁማዳ ከፍ ካለ ስፍራ
መጥቆ እንደባልዲራ
ምንም ባዶ ቢሆን በውስጡ አይጠፋና የታሪክ አዝመራ።"
ይህንን ተናግሮ ከአክሱም ሐውልት ዘንድ ትግራይ ተጠግቶ
አንዴ እየፀለየ አንዴ እየዘመረ ያለመጠን ተግቶ
ጫፉ ላይ ሰቀለው ያን አቁማዳ አውጥቶ።

1967



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

*የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ*
*ሚያዝያ16,1999ዓ.ም*

## ዛሬን እንኳን

እስቲ ዛሬን
        ዛሬን እንኳን
        ዛሬን እንኳን ሣቂ፤
እስቲ ዛሬን
        ዛሬን እንኳን
        ዛሬን እንኳን ፍንጭትሽን አትደብቂ፤
        አትደብቂ - ፈገግታሽን አትፋቂ።
ጐረቤት አይታዘብሽ
የሐሴት ደመኛ እያርግሽ
እባክሽ፤ እናት ዓለም እባክሽ።
የዕጣሽን አድማስ ጉም ሸፍኖት
ምድር ሰማይሽን አጨልሞት
ፀሐይሽን ቢጦልብሽ
ጨረቃሽን ቢሠርቅብሽ
አንቺ እማዬ እንደ ሌሎች፤ መሣቅን እማታውቂ ነሽ?
በዕንቁጣጣሽ ዋዜማ ድንኳን
በተቀጣጠለው ችቦ ውጋጋን
ፈካ ይበል የገጽሽ ብርሃን
ደመቅ ይበል የልብሽ ዙፋን
ዛሬን እንኳን፤
        እማምዬ
                ዛሬን እንኳን።
ለኛም ችቦ አዳርሰሽን፤ ኢዮሃ እበባዬ እንበል
በውሃ አይደል፤ ዛሬስ በቃል በሁካታ እንጠበል።
ተቻንክሮ እንደኖረ በር፤ በትግላችን ተለማምጠን
አንደበታችንን ተማጽነን፤ ከንፈራችንን አላቀን
ቢጐለድፍ መላሳችን፤ ባይጥም እንኳን ዜማችን



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የደበበ ሰይፉን 7ኛ ዓመት የሙት ዓመት ምክንያት በማድረግ የተቀናበረ ሚያዝያ16,1999ዓ.ም

ቢሰባበር ድምፃችን፣ ዝርው ቢሆን ነገራችን
ብቻ እንጩህ ፍቀጅልን - ጩኸት ነው እኛን ያማረን።
እውን ጩኸት ነው እኛን ያማረን፣ በጩኸት እንበልበል
የገደል ማሚቶ ትንቃ፣ ከአንቅልፍ ትራሷ ትከንበል
ከቦዘን ሕልሟ ትፈንገል።
አንደበታችንኮ ዝጓል እማምዬ፣ አፅምሯችንን በክሎ
ቃል አስጥሎ ሐሳብ ገድሎ
ያይንን እውነት በእርምሞ አሰልስሎ
የጆሮን ታሪክ በዝምታ አብጠልጥሎ
አንደበታችንኮ ዝጓል እማምዬ፣ አእምሯችንን በክሎ።
የጣር የጭንቅ ድምፃችን፣ እንደ አምቃ ዛሬ ይድረስሽ
የዘመናት ቅርሳችን፣ ውጥቶ ፊትሽ ይቅረብልሽ
የፍሬያችን የምሥራች ከቶ ምን ቢሆን አንነፍግሽ።
ከኛ ፈገግታ አትጠይቂ
ከኛ ሐሴት አትጠብቂ
እንባም ለኛ ተስፋ ነው፣ እባክሽ ስለ እንባችን አንቺ ሳቂ
        አንቺ፣ ስለ ጩኸታችን ፈንድቂ
        አንቺ፣ ስለ ጭንቅ ድምፃችን ቦርቂ።
አለመሣቀኮ ይቻላል፣ አለማልቀስ ነው ጭንቁ
የመንፈስን እንጉርጉሮ፣ በመንፈስ አምባ ማመቁ
ውስጥ ውስጡን እየደሙ፣ በቀቢፀ - ተስፋ መድቀቁ
ለተስለመለመች እውነት፣ የደም ደብዳቤ ማርቀቁ
በቅሬታ ሰደድ እሳት፣ ሕዋሳትን መጨፍለቁ፣
አለመሣቀኮ ይቻላል፣ አለማልቀስ ነው ጭንቁ።
እና፣ እስቲ ዛሬን
                ዛሬን እንኳን
                ዛሬን እንኳን ሣቂ፣
እስቲ ዛሬን
        ዛሬን እንኳን
        ዛሬን እንኳን ፍንጭትሽን አትደብቂ፣
        አትደብቂ - ፈገግታሽን አታርቂ።

        ሚያዝያ 1966ዓ.ም.



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com